# ቋንቋ እና ቅኝ-ግዛት: አነስተኛ ተናጋሪ ያላቸው ቋንቋዎች በዲጂታል ዓለም ውስጥ



“

**የአፍ መፍቻ ቋንቋዎትን ካወቁ እና ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር ካዛመዱት በሚገባ ያጎለብቱታል**

**ንጉጊ ዋ ቲዮንጎ**

ይህ ፕሮጀክት የተከናወነው በትልቅ ድጋፍ ነው

Internet Society Foundation

POLLICY

Meital K. and Jason M. (2022) Language and Coloniality: Non-Dominant Languages in the Digital Landscape. Pollicy.

# ማውጫ

01 መግቢያ

02 የችግሩ መነሻ

04 የጥናቱ ዓላማ

05 ትርጉሞች

06 የጉዳይ ጥናቶች

07 ኢትዮጵያ

13 ታንዛኒያ

17 ኡጋንዳ

22 የቅኝ ግዛትና የቋንቋ ውርስ በበይነመረብ ላይ

23 የእርምጃ ጥሪ

24 ማጠቃለያ

26 ዋቢዎች

# መግቢያ

በዲጂታል ዓለሙ ላይ ህያው የሆኑ ወይም የሚገኙ ወደ 29 የሚጠጉ ቋንቋዎች ብቻ ይገኛሉ (ሲሞንስ እና ሌሎች.,2017)። ዲጂታል ህያውነት (digital vitality) አንድ ቋንቋ በምን ያህል መጠን በበይነመረብ ላይ እና በዲጂታል መገልገያ መድረኮች ላይ ጥቅም ላይ እንደሚውል ያሳያል። ብዛታቸው አስር የሆኑ ቋንቋዎች ሰማንያ-ሁለት በመቶውን የኢንተርኔት ይዘት ይወክላሉ እነዚህም እንግሊዝኛ፣ ቻይንኛ፣ ስፓኒሽ፣ አረብኛ፣ ፖርቹጋል፣ ጃፓንኛ፣ ራሽያ፣ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ እና ማሌዥያ ናቸው (የኢንተርኔት ዎርልድ ስታቲስቲክስ እንደሚያሳየው) ። ዲጂታል መድረኮች፣ መተግበሪያዎች እና ሶፍትዌሮች ለ "አናሳ" ወይም ብዙ ተናጋሪ ለሌላቸው ቋንቋዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖራቸው እንደ እንግሊዝኛ ካሉ ቋንቋዎች ውጪ ያሉ ተናጋሪዎችን የኑሮ ተሞክሮ ያሳያል።

በዲጂታል ዓለም ላይ ያለው የቋንቋ ብዝሃነት ማነስ ብዙ ተናጋሪ የሌላቸው ቋንቋዎችን ተጠቃሚነት ማሽቆልቆል ያሳያል። የተለያዩ ቋንቋዎች በዲጂታል መድረኮች ላይ ጥቅም ላይ የማይውሉ ከሆነ ተጠቃሚዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የዓለም የዕለት ተዕለት ህይወት አካል የሆኑ ማህበራዊ ሚዲያዎች፣ ኢ-ኮሜርስ እና ሌሎች የኢንተርኔት አገልግሎቶችን የመጠቀም አቅማቸው አናሳ እንዲሆን ያደርጋል። በይነ-መረብ ላይ የሚኖር የመፃፊያ ዘዴ/ፊደል ወይም ቋንቋ ከፅሁፍ ፊደሉ ወይም ከቋንቋው መኖር ባሻገር የግብዕትና የውጤት አቅም ሊኖረው ይገባል፤ ግብአት ማለት ተጠቃሚው በብዛት በዲጂታል መድረኮች ላይ የሚያገኘው ቋንቋ ሲሆን ውጤቱም ተጠቃሚው ጥቅም ላይ የሚያውለው ቋንቋ ነው። (ኮርናይ፣ 2013) ። በይነ-መረብን መካከለኛ በሚባል ደረጃ የሚጠቀሙ ተገልጋዮችን የኑሮ ተሞክሮ በተሻለ ሁኔታ መረዳትና ተጨማሪ ቋንቋዎችን በዓለም አቀፍ የበይነ-መረብ መድረክ ላይ ማካተትና ማዋሀድ የምንችለው እንዴት ነው?

# የችግሩ መነሻ

ሥራዎቹን ከእንግሊዝኛ ይልቅ በኪኩዩ ቋንቋ በመጻፍ የሚታወቀው ንጉጊ ዋ ቲዮንጎ የተባለው ዕውቁ ኬንያዊ ፀሃፊ የሀገር በቀል ቋንቋን በመተው እንደ እንግሊዘኛ ባሉ የአውሮፓ ቋንቋዎች መፃፍን በመቃወም ይሞግታል። ዲኮላንይዚንግ ዘ ማይንድ (Decolonising the Mind (1986)) በተባለው መፅሀፉ የአፍሪካ ባህል ለምን በአውሮፓ ቋንቋዎች እንደሚቀመጥና እንደሚተረጎም ይጠይቃል። ቲዮንጎ ሁሉንም ፅሁፎቹን በቢኩዩ ቋንቋ ለማሳተም መወሰኑ ለዘመናት ከተጫነው ልማድ መውጣትንና ራስን በራስ ማንነት የመግለፅ ፅኑ ፍላጎትን ያሳያል።

ይህም አሁን ባለው የዲጂታል ዓለም ላይ የሚንፀባረቅ ነው። ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት እና በሰፊው ግሎባል ደቡብ የሚገኙ ሀገራት የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎቻቸውን በበይነ-መረብ እየከወኑ በመጡ ቁጥር በስፋት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቋንቋዎችን እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ። የበይነ-መረብ ተደራሽነት ስንል መገልገያ መሳሪያንና ገመድ አልባ የኢንተርኔት አገልግሎትን ከማግኘት ከፍ ያለ ትርጉም ያለው ሲሆን የቋንቋ ብዝሃነትን ያማከለ ተደራሽነትም ያካትታል። የዲጂታል መድረኮች አናሳ የተናጋሪ ቁጥር ያላቸው ቋንቋዎችን ያገለሉ ናቸው። እነዚህ መድረኮች ሶፍትዌርና መተግበሪያዎችን ጨምሮ ብዙ ተናጋሪ ላላቸው ቋንቋዎች ተብለው የተዘጋጁ ናቸው። ይህም እንደየአዉዱ የሚለያይ ነው፡- እንደ ሂንዲ (ህንድ) እና ማንዳሪን (ቻይና) ያሉ ቋንቋዎች በማህበራዊ እና ዲጂታል አውድ ውስጥ የበላይነታቸውን እያገኙ ሲሆን እንደ ስዋሂሊ (ምስራቅ አፍሪካ) እና ዮሩባ (ናይጄሪያ) ያሉ ቋንቋዎች ደግሞ ከዲጂታል ይልቅ በአካል የሚደረጉ መስተጋብሮች ላይ የበላይ ናቸው።

በቋንቋ ረገድ የሚታየው የቴክኖሎጂ ዕድገት እኩል አይደለም። በአይፎን እና በሌሎች የአፐል ምርቶች ላይ የሚገኘው ሲሪ የተሰኘው መተግበሪያ በ25[1] ቋንቋዎች ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን ከቻይንኛ፣ ጃፓንኛ፣ ኮሪያኛ እና አረብኛ በስተቀር አብዛኞቹ የአውሮፓ ወይም የላቲን ቋንቋዎች ናቸው። በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ደግሞ የትዊተር ድረ-ገፅ እንደ ሂንዲ፣ ማላይኛ፣ ፊሊፒኖ እና ቬትናምኛ ያሉ ተመሳሳይ መገኛ ያላቸውን 34 ቋንቋዎች ይጠቀማል።[2] አብዛኛዎቹ የማህበራዊ መገናኛ መድረኮች እንግሊዝኛን እንደ ዋና ቋንቋቸው ይጠቀማሉ፤ ይህም እንግሊዝኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያልሆኑትን ጨምሮ ሰማንያ ሁለት በመቶ ተጠቃሚዎችን ያጠቃልላል (ክሪስትሰን እና ሙሬይ፣ 2014)። ነገር ግን ሀገር-በቀል ወይም አናሳ ተናጋሪ ያለውን ቋንቋ እንደ ዋና ቋንቋው ለሚናገር ተጠቃሚ ተደራሽነቱ ውስን ነው። በድረ ገፃቸው ላይ በሚቀርቡት አግባብነት የሌለው እና በቂ ያልሆነ ይዘት ምክንያት ሀገር በቀል ቋንቋዎችን ጥቅም ላይ የሚያውሉ ድረ-ገፆችን የማግኘት እድልም የተገደበ ነው። ኩባንያዎችም ቢሆኑ በሀገር-በቀል ቋንቋዎች የሚዘጋጁ ድህረ-ገፆችን በንግድ ስራቸው ላይ አያካትቱም። አብዛኛዎቹ አናሳ የተናጋሪ ቁጥር ላላቸው እንደ ማኒቶባ፣ ካናዳ ተወላጅ ቋንቋ ተናጋሪዎች የተዘጋጁ የማህበራዊ ሚዲያ ድረ-ገፆች በራሳቸው በተጠቃሚዎች የተሰሩ ናቸው።[3]

በበይነ-መረብ ላይ የሚታየው የቋንቋ ልዩነት እያደገ የመጣውን የዲጂታል ክፍፍል ያንፀባርቃል። ይህም በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) እና የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነት ባላቸውና በሌላቸው መካከል ባለው ልዩነት የተስተዋለ ነው (ኩለን፣ 2001)። ብዙ ተናጋሪ ያላቸው ቋንቋዎችን የማይናገሩ ተጠቃሚዎች በዲጂታል ክፍፍል ውስጥ በእጅጉ ወደ ኋላ እንዲቀሩ ሆኗል። የዲጂታል ቋንቋ ክፍፍል እንደሚያሳየው አሁን ከምንናገራቸዉ 6,000 ቋንቋዎች መካከል 82 በመቶውን የኢንተርኔት ይዘት የሞሉት አስር የሚሆኑት ብቻ ናቸው (ያንግ, 2014)።

በአጠቃላይ በይነ-መረብ እና ተያያዥ ዲጂታል መድረኮች ላይ የቋንቋ ተካታችነት አናሳ ነው። ይህ ወደ አንድ ቋንቋ የበላይነት የሚደረገው ሽግግር የቋንቋ ብዝሃነትን እየቀነሰ እና በዲጂታሉ ዓለም አናሳ ተናጋሪ ባላቸው ቋንቋዎች ለመግባባት ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ተጨማሪ እንቅፋቶችን እየፈጠረ እንደሆነ ያሳያል።

---

[1] https://www.apple.com/ios/feature-availability/#siri
[2] https://developer.twitter.com/en/docs/twitter-for-websites/supported-languages
[3] https://guides.wpl.winnipeg.ca/indigenouslanguages/home

# የጥናቱ ዓላማ

ሀገር-በቀል ቋንቋዎች በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ያሉትን ቁልፍ ጉዳዮች እንዳስሳለን። እነዚህም በዲጂታል ክፍፍል ጭብጥ ላይ ተመስርተው የሚነሱ የዲጂታል እኩልነት፣ ተሳትፎ፣ ዜግነት፣ ባለቤትነት እና ማንነት ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ናቸው። በዚህ ጥልቅ ትንተና ቋንቋ በዲጂታል መድረኮች ላይ መካተቱ የተጠቃሚ ተሳትፎን እንዴት እንደሚያበረታታ፣ እንደሚገድብ፣ እንደሚያሰፋ እና እንደሚያበለጽግ ለመረዳት እናልማለን። እንዲሁም በይነ-መረብን መካከለኛ በሚባል ደረጃ የሚጠቀሙ ተጠቃሚዎች በእነዚህ ዓውድ ውስጥ ዲጂታል መድረኮችን ለግንኙነት እና ለዕለት ተዕለት ኑሮ ሲጠቀሙ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን የተደራሽነት፣ደህንነት እና አጠቃቀም ጭብጦች እንመለከታለን።

# ትርጉሞች

የዲጂታል ቅኝ ግዛት፡- የዲጂታል ቴክኖሎጂን ለሌላ ብሔር ወይም ግዛት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ የበላይነት መጠቀም (ይመልከቱ፡ Kwet, 2016)።

ዲጂታል ክፍፍል፡- በብዙ ሀገራት የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) መሣሪያዎች ተደራሽነት ባላቸው እና ባገኙት ዕውቀት እና ይህን መሰል ተደራሽነት ወይም ዕውቀት/ችሎታ በሌላቸው መካከል ያለው ክፍተት ነዉ (ይመልከቱ፡ ኩለን፣ 2001)።

ዲጂታል ህያውነት፡- አንድ ቋንቋ በይነመረብ ላይ በዲጂታል መሳሪያዎች እና መድረኮች በምን ያህል መጠን ጥቅም ላይ ይዉላል የሚለውን ያሳያል።

የዲጂታል ቋንቋ መሞት፡- በዲጂታል መድረኮች በምንጠቀማቸው ቋንቋዎች ላይ የሚከተሉት ሲያጋጥሙ፡
አስፈላጊነቱን ማጣት፡ አንድ ቋንቋ በዲጂታል መድረክ፣ በዕለት ተዕለት ግንኙነት (የጽሑፍ መልዕክት፣ ኢሜል) ለንግድ እና ለመሳሰሉት ጥቅም ላይ የማይውል ከሆነ
ያለውን ቦታ ማጣት፡- አንድ ቋንቋ በበይነ-መረብ በትንሽ መጠን ወይም ምንም የማይዘወተር ከሆነ
ብቃቱን ማጣት፡ የዲጂታሉ ዘመን ተጠቃሚዎች ቋንቋውን አቀላጥፈው የማያውቁት ከሆነ

ሀገር በቀል ቋንቋ፡- የአንድ ክልል ተወላጅ እና ተመሳሳይ ባህላዊ እሴት እና እምነት ያላቸው ተወላጆች የሚናገሩት ቋንቋ ወይም የቋንቋ ስብስብ ነው።

ብዙ ተናጋሪ ያለው ቋንቋ - በአንድ ሀገር ውስጥ አብዛኛው ህዝብ የሚጠቀምበት ቋንቋ ነው። ይህ ምናልባት በበላይነት የተጫነ (ንጉሳዊ) ቋንቋ (ለምሳሌ- እንግሊዘኛ ቋንቋ በኡጋንዳ) ወይም ሀገር በቀል ቋንቋ (ለምሳሌ- ሂንዲ ቋንቋ በህንድ) ዓይነት ሊሆን ይችላል።

# የጉዳይ ጥናቶች

በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው የዲጂታሉ ዓለም እና ቋንቋ ያላቸውን ግንኙነት የበለጠ ለመረዳት የሶስት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት (ኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ እና ኡጋንዳ) ጥናት አቅርበናል። በዚህ ግምገማ ሦስት ዋና ተያያዥ ጭብጦች አሉ። በመጀመሪያው ተደራሽነት እንመለከታለን። አነስተኛ ተናጋሪ ያላቸው ቋንቋ ተናጋሪዎች ሕይወትን ‘‘ቀላል’’ ለማድረግ በሌላ ቋንቋ ፊደል የራሳቸውን ቋንቋ በመፃፍ ወይንም እንደ እንግሊዝኛ ባሉ ቋንቋዎች ይጠቀማሉ? በዲጂታል መድረኮች ላይ አንዳንድ ቋንቋዎች ከሌሎች ይልቅ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል? በዲጂታል መድረኮች ውስጥ የተወሰነ ቋንቋ(ዎች) ከመጠቀም ጋር የተያያዘ ማህበራዊ ግንኙነት/ትስስር አለ?

በሁለተኛ ደረጃ አጠቃቀምን እንመለከታለን፡፡ ተጠቃሚነት በኮርናይ (2013) በተገለፀው የቋንቋ አጠቃቀም ተያያዥ ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ነው።

(1) ቋንቋውን የሚናገረው ማህበረሰብ መጠን እና ስነ-ሕዝብ ስብጥር;
(2) ለቋንቋው የሚሰጠው ቦታ/ክብር;
(3) ቋንቋው ማንነትን ለመግለጽ ያለው አገልግሎት
(4) የሶፍትዌር ድጋፍ ደረጃ (the level of software support) እና
(5) ውክፔዲያ (Wikipedia) ናቸው።

የተለየ ቋንቋ ተናጋሪዎች የተለያዩ ሶፍትዌሮችን፣ መተግበሪያዎችን እና አገልግሎቶችን በቀላሉ መጠቀም መቻላቸውን እናጠይቃለን። ይህ በተለየ መልኩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የላቲን ፊደላትን የማይጠቀሙ ሀገራትን ይመለከታል። ብዙ ተናጋሪ የሌላቸው ቋንቋ ተናጋሪዎች በዲጂታል መድረኮች ላይ በራሳቸው ቋንቋ መጠቀም፣ መስተጋብር መፍጠር እና ይዘቶችን ማተም ይችላሉ? ቃላት ማስተካከያ መዝገበ ቃላት መሳሪዎች (Auto correct) ወይም አኤስ ወይም የግብአት ደረጃ መተግበሪያ በሀገር በቀል ቋንቋ ተዘጋጅቷል?

በመጨረሻም ደህንነት በተደጋጋሚ የሚነሳ ቁልፍ ጉዳይ ነው። አነስተኛ ተናጋሪ ያላቸው ቋንቋ ተጠቃሚዎች በይነመረብ በመጠቀማቸው ምክንያት መገለል ወይም ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችል መሆኑን እናጠይቃለን። በተመሳሳይ አንዳንድ ቋንቋዎች ይዘታቸው የሚፈተሸው ወይም የሚገመገመው ከሌሎች ብዙ ተጠቃሚ ካላቸው ቋንቋዎች የበለጠ ነዉ ወይንስ ያነሰ ነው? በዲጂታል መድረኮች ላይ ከቋንቋ ጋር የተያያዙ አንዳንድ የተዛቡ አመለካከቶች (stereotypes) አሉ? የሚሉትን ጉዳዮች እናጠይቃለን።

# ኢትዮጵያ

ወልደማርያም እና ላንዛ (2014) ኢትዮጵያን “የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች እና የባህል ብዝሃነት” ያለባት ሀገር መሆኗን ይገልፃሉ። የአገሪቱ የ114 ሚሊዮን ህዝብ መንግስት - ከ80 በላይ ብሔረሰቦችን ያቀፈ ሀገር ቢሆንም - ለአምስት ቋንቋዎች ማለትም አፋርኛ፣ አማርኛ ፣ ኦሮሞኛ፣ ሶማሊኛ እና ትግርኛ የአገሪቱ ይፋዊ የስራ ቋንቋዎች እንዲሆኑ እውቅና ሰጥቷል። ነገር ግን ከዚህ ባለፈ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን፣ የመንግስትን እና የመገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ በአጠቃላይ 28 ቋንቋዎች በተለያዩ ህዝባዊ እርከኖች ታሪክ ውስጥ ይገኛሉ። አማርኛ ግን የአገሪቱ ቋንቋ ነው፣ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ቋንቋውን ይረዳዋል እንዲሁም ይናገረዋል። ይህም የሆነው በአብዛኛው የ20ኛው ክፍለ ዘመን የሀገሪቱን ታሪክ በበላይነት በያዙት ገዥዎች አማካኝነት ሊሆን ይችላል። (ዩሱፍ፣ 2019) ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ተገዝታ አታውቅም፣ ስለዚህም የማህበረሰብ ቋንቋ ስሪቷ የተቀረፀው በብሔር ብሔረሰቦች እራስን በራስ የማስተዳደርን ጥያቄ ቀጣይነት ባለው የለውጥ ሂደት ነው።

የኢትዮጵያ የቋንቋ ፖሊሲ በጣም ተራማጅ ነው (ዩኒሴፍ፣ 2016) ። አገሪቷ ለብዙ ዘመናት የብሔር ብሔረሰቦች ማህበረሰብ ሆኖ ሳለ፣ አሁን ያለው የቋንቋ ገጽታ መነሻ ግን በ1995 (እ.ኤ.አ.) መንግስት በይፋ የጀመረው የብሔር ፌደራሊዝም አካሄድ ነው ሊባል ይችላል (ታዬ፣ 2017)። የሀገሪቱ ዋና ዋና ብሔረሰቦች ጥምር መንግስት ባመጣው በዚህ አዲስ ስርዓት፣ ቋንቋዎች የብሔር ብዝሃነትን ለማንፀባረቅ እና ለማስተዋወቅ በክልል ያተኮሩ ነበሩ (ወልደማርያም እና ላንዛ፣ 2014) ። ይህ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት (1930 - 1974) እና ተከታዩ የማርክሲስት ሌኒኒስት የደርግ መንግሥት (1974 - 1991) (ዩሱፍ፣ 2019) የተካሄደውን አምባገነናዊና አፋኝ የቋንቋ ፖሊሲዎች በግልፅ ውድቅ ያደረገ ነበር።
በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፣ በጋራ ማንነት የተሳሰረችውን ሀገር አንድ ለማድረግ ታስቦ በነበረው የፖለቲካ ፕሮጀክት፣ አማርኛ የአገሪቱ ቀዳሚ የበላይ ቋንቋ ሆኗል። የሌሎች ቋንቋዎች መስፋፋት ለብሔር ቅስቀሳ መግቢያ በር ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ በጊዜው የሚወጡት ፖሊሲዎች የቋንቋዎቹን ዕድገት እንዲገድቡ ሆነው ነበር። የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለምን የያዘው ወታደራዊ መንግሥት - ደርግ ንጉሣዊውን ሥርዓት ሲገረስስ የክልል ቋንቋዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል እንቅስቃሴ አድርጓል። በሀገር አቀፍ ደረጃ በተተገበረው የትምህርት ዘመቻ ወቅት ሰዎች በአገራቸው ቋንቋ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ለማስተማር ተሞክሯል፤ ለዚህም ዓላማ 15 ቋንቋዎች ጥቅም ላይ ውለው ነበር (ጌታቸው እና ደርብ፣ 2006) ። ይህ የተስፋፋ አካሄድ ቢኖርም የአማርኛ የበላይነት በብዙ ምክንያቶች ቀጥሏል፡- 1. ማዕከላዊውና ከላይ ወደ ታች የተዘረጋው የመንግስት ስልጣን በባህሪው አግላይ ነበር፣ 2. የተገነቡት አማራጭ የቋንቋ ምንጮች የጥራት ደረጃ ደካማ መሆን እና 3. ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች አማርኛ ተናጋሪዎችን በተሻለ የሚጠቀሙ መሆናቸው (ስሚዝ፣ 2008)። በ1991 ዓ.ም የሀገሪቷ አስተዳደር ስርዓት ከማዕከላዊ አካሄድ ወደ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ሲሸጋገር የሀገሪቱን ማህበራዊ ትስስር ለማስቀጠል በተደረገው ጥረት ሁሉም ህዝቦች የጋራ መግባባት እንዲኖራቸው እና ማንነታቸውን እንዲገልጹ ወደሚደረግበት የብሔር ራስን በራስ ማስተዳደር ሰርዓት ቅድሚያ ወደ መስጠት ተሸጋግሯል (ሀብቱ፣ 2003)። የብሔር ቋንቋዎች በብሔራዊ ቋንቋ ፖሊሲ መግለጫ የትምህርት ክፍል አማካኝነት ተዋውቀዋል (ስሚዝ፣ 2008)። በቀጣይነት ደግሞ በ1994 ዓ.ም ይፋ በሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (NETP) እና በ1995ቱ ህገ መንግስት ተካቷል። ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ የመማር መብት እና በሌሎች የሀገሪቱ kንkዎች

ፊት እኩል የመታየት እውቅና ተሰጥቷቸዋል (ስሚዝ፣ 2008፣ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት፣ 1995፣ የኢትዮጵያ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1994)። ይህም ክልላዊ እና አካባቢያዊ ቋንቋዎች በህዝባዊ ቦታዎች ታይታቸው እንዲጨምር አድርጓል፣እንዲሁም በርካታ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎችም ጉልህ ዕድገት እንዲኖራቸውና እና በብዙ መድረኮች ላይ መገኘታቸው እንዲጨምር አድርጓል (ወልደርማርያም እና ላንዛ፣ 2014) ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አማርኛ የሀገሪቱ የስራ ቋንቋ ሆኖ ቆይቷል፣ ይህም በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል አድርጎታል። ነገር ግን፣ በሀገሪቱ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የጎሳ ግጭት ምክንያት የኢትዮጵያ መንግስት የሀገሪቱን የፖለቲካ የበላይነት የሚያሳዩ ብሔረሰቦችን የሚያንፀባርቁ አራት ተጨማሪ የስራ ቋንቋዎችን ጨምሮ ተከታታይ ማሻሻያዎችን አድርጓል።

በኢትዮጵያ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውለው የውጭ ቋንቋ እንግሊዝኛ በመደበኛነት ወደ ሀገሪቱ የገባው በትምህርት ሥርዓቱ ነው (ሻርማ፣ 2013) ። በአፄ ሀይለ ሥላሴ ዘመን ከትምህርት ዘርፍ ጋር በተያያዘ በተለይም በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዙሪያ ለቋንቋው ዕውቅና ተሰጥቶ ነበር። ይህ የተካሄደበት ጊዜም “ወርቃማው የትምህርት ዘመን” ተብሎ ይጠቀሳል፣ ይህም በከፊል በመላ አገሪቱ ባሉ ትምህርት ቤቶች ፈጣን እድገት የታየበት በመሆኑ ነው (ጌርንቼል እና ሚሽራ፣ 2019)። በወቅቱ የነበረው የትምህርት ስርዓት የእንግሊዝ እና አሜሪካ ተጽዕኖ ነበረበት፣ በዚህም ለእንግሊዝኛ kንk በተሰጠው ትልቅ ቦታ ምክንያት ሰፊ ተቀባይነት አግኝቷል። ከአማርኛ kንk ጎን ለጎን የእንግሊዝኛ እውቀት ለብሔራዊ ፈተናዎች እና በወቅቱ የሀገሪቱ ብቸኛ ወደሆነው ዩኒቨርሲቲ ለመቀላቀል እንደ ግዴታ ተቀምጦ ነበር። (ስሚዝ 2008)። ብሔራዊ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (NETP) ሥራ ላይ ከዋለ በ|ላ፣ የብሔር ቋንቋዎች ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማስተማሪያ ሆነው ሳለ እንግሊዝኛ እንደ መማሪያ kንk ሆኖ ቆይቷል። በተለይም ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ባለፈ የመማሪያ ቋንቋ ሆኖ ቆይቷል። በአሁኗ ኢትዮጵያም እንግሊዝኛ በሰፊው የሚነገርና ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የውጭ አገር ቋንቋ መሆኑን ቀጥሏል (Gerencheal & Mishra, 2019) ። ምንም እንኳን ይህ ሰፊ ፍላጎት ቢኖርም፣ እንግሊዝኛ በተወሰኑ ጎራዎች ብቻ ተወስኗል። በብዛት ጥቅም ላይ የሚውለው በተማረው የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ነው፣ አጠቃቀሙም በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ የተወሰነ ነው (ጌርንቼል፣ 2016፣ ሻርማ፣ 2013)። በመምህራንና ተማሪዎች ዘንድ የእንግሊዝኛ ቅልጥፍና (fluency) ዝቅተኛ ነው፣ ብዙዎች በቋንቋው መጠቀም ስለሚኖርባቸው ሲጨነቁ ይስተዋላል።

ዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ እንደሆነ ይገመታል (ቀናው፣ 2017)። መሰረቱ በቀደሙት መንግስታት እንደ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የስልክና የቧንቧ ውሃ አቅርቦት ሲስፋፋ የተጣለ ቢሆንም ሀገሪቱን በማዘመን ትልቅ ዕድገት ያስመዘገቡት አፄ ሀይለስላሴ ነበሩ። ከውጭ የገቡት ቴክኖሎጂዎች ንጉሡ ነገሥቱ ሥልጣናቸውን እንዲያጠናክሩና ዘመናዊ የትምህርት ሥርዓት እንዲጎለብት ያላቸውን ምኞት ለማሳካት አስችሏቸዋል። ነገር ግን አፄ ሃይለስላሴ ለቴክኖሎጂ ማዘመን ያደረጉት ጥረት ከቀደምት (ቶች) ጋር በሚመሳሰል መልኩ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጥያቄ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ግልፅ አይደለም። ይልቁንም በጊዜው ተስፋፍቶ የነበረው ቴክኖሎጂ ከውጭ እንዲገባና ወደ ሀገር እንዲቀላቀል የተደረገው ቃላቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ቋንቋዎች  መተርጎምን በመሰሉ መንገዶች ነው (ቀናው፣ 2017)። ቀደም

ሲል እንደተገለፀው እንግሊዝኛ የንጉሠ ነገሥቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቋንቋ ተብሎ ስለሚታሰብ ወደ ትምህርት ሥርዓቱ እንዲካተት አድርገውታል። በ1991 ዓ.ም የክልሎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ለብሔር ብሔረሰቦች ሲሰጥ የሀገሪቱ በቁጥር ትልቁ ብሔር የሆነው የኦሮሞ ቋንቋ ንቅናቄ መሪዎች የፅሁፍ ፊደላቸው ከግዕዝ ወደ ላቲን ፊደል በከፊል እንዲቀየር ከዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ባገኙት ድጋፍ ማድረግ ችለዋል (ይማም (1992) በዛውግ፣ 2020) ። እነዚህ ተለዋዋጭ ሂደቶች በኢትዮጵያውያን፣ በቋንቋዎቻቸው እና በቴክኖሎጂው መካከል ያለውን የግንኙነት ሂደት ጠkሚዎች ተደርገው ሊታዩ ይችላሉ። አማርኛን እንደ የበላይ የሀገሪቷ ቋንቋ (እንዲሁም ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን) በዲጂታል መድረኮች ላይ ማካተትን የበለጠ ለመገምገም በተደራሽነት፣ አጠቃቀም፣ አመለካከት እንዲሁም በደህንነት መመዘኛዎች መገምገም ይቻላል።

ወደ አካታችነት ስንመጣ, አማርኛ የተስፋፋ ቢሆንም እንደ ዝቅተኛ ቋንቋ ተመድቧል (ገረመ ኢ.ቲ. ኤኤል., 2021) ። ውስን የሆነ ዲጂታል ሀብቶች ያላቸው ቋንቋዎች ዝቅተኛ-ምንጭ ቋንቋ በመባል ይታወቃሉ (ሜጌርዱሚያን እና ፓርቫዝ, 2008; ሆጋን, 1999) ። ግዕዝ በመባል የሚታወቀው የኢትዮፒክ ፊደል የአፍሪካ ጥንታዊ ፊደል ነው። አማርኛ እና ትግርኛ ተናጋሪዎች የሚጠቀሙት ሲሆን ፊደሉን,ቅርፁን ሌሎች አነስተኛ ተናጋሪ ያላቸው ቋንቋዎች በትንሽ ማሻሻያ በሚያስተናግድ መልኩ ይጠቀሙታል። ከሌሎች ላቲን ያልሆኑ የአፍሪካ ቋንቋዎች ጋር ሲወዳደር ግዕዝ ባለፉት 40 ዓመታት በተለይ በበይነመረብ ላይ ከፍተኛ እድገት አስመዝግቧል (ዛውግ, 2020) ። የተለያዩ ፈጠራዎች እና እንቅስቃሴዎች እየተስተዋሉ ሲሆን አንዳንዶቹ በበለጠ ስራ የሚፈልጉ ናቸው። ከ1980ዎቹ ጀምሮ በግዕዝ ላይ የተመሰረቱ ቋንቋዎች ስክሪፕቱን ሲጠቀሙ በዲጂታል ድጋፍ የቃላት ማቀነባበሪያዎች (word-processors) በፎንትና በኪቦርድ እንዲሁም በ1999 በዩኒኮድ ደረጃ (ዩኒኮድ ስታንዳርድ) ውስጥ አካቶ በኩል ተጠቃሚ ሆነዋል። የዚህ ሥራ ትልቁ ድርሻ በኢትዮጵያውያን የቋንቋ ሊቃውንት የተከናወነ ነው። ምንም እንኳን በቋሚነት ባይሆንም ዓለም አቀፋዊ ጥረትም ለዕድገቱ አስተዋፅኦ አሳይቷል። እ.ኤ.አ. በ2010 ማይክሮሶፍት ዊንዶ ቪስታ የተባለውን ኦፐሬቲንግ ሲስተሙን (Operating system) በአማርኛ አስጀመረ (ሶማሊላንድ, 2010)። እ.ኤ.አ. ከ 2015 ጀምሮ አማርኛ በተለያዩ የጎገል ስዊት (Google Suite) ምርቶች ላይ፣ የበይነመረብ ፍለጋ ፣ ከንግግር ወደ ጽሑፍ አገልግሎት (Cloud Speech API) ጨምሮ ይገኛል (ፔሬዝ, 2017 ጋልፐሪን, 2014)።
ሳሲኩማር እና ሄጅ (2004) የሃገር በቀል ዕንቅስቃሴን በአራት ምድቦች ከፋፍለውታል፡ 1. ማሳያ (የአከባቢው ስክሪፕት መኖር) ፣2. ቋንቋ (በአካባቢው ቋንቋ የስርዓት ጽሑፍ መገኘት) 3. ባህል (ከባህል ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን አውዶች መጠቀም) 4. መሳሪያ (አውዳዊ የመሳሪያ አጠቃቀም)

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረጉት የአካባቢያዊነት ጥረቶች አብዛኛዎቹ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምድቦች ማለትም ማሳያ እና ቋንቋን ያካተቱ ናቸው።
አፕል የተባለው የቴክኖሎጂ ድርጅት የመጀመሪያውን በአማርኛ የተገነባ (ግዕዝ) ቁልፍ ሰሌዳ ያስተዋወቀው እ.ኤ.አ በ2021 የአይፎን ኦፐሬቲንግ ሲስተም(IOS) 15ን ከለቀቀ በኋላ ነው።
ምንም እንኳን ጥሩ ጅምር ቢሆንም የቁልፍ ሰሌዳ (ኪቦርድ) የተጠቃሚውን ልምድ በሚያደናቅፉ እና አጠቃቀሙን

በሚያሰናክሉ ተግዳሮቶች የተሞላ ነው። እንደ የመሠረተ ልማት ውሱንነት፣ የዋጋ ንረት እና በመንግስት የተደነገጉ ህግጋት ያሉ ኢትዮጵያውያን በበይነመረብ ላይ እንዳይገቡ የሚያደርጓቸው የተደራሽነት ተግዳሮቶች እንደቀጠሉ ናቸው (ሻህባዝ እና ፋንክ, 2020)። በተጨማሪም በይነ-መረብ ላይ ከአማርኛ ውጭ ያሉ ተናጋሪዎች ከአማርኛ ተናጋሪ አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀሩ ፈታኝ በሆነ የቴክኖሎጂ ቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ ይገኛሉ።  በኢትዮጵያ ውስጥ ከ80 እስከ 90 በመቶ የሚሆነውን የድረ-ገፅ ይዘት እንግሊዝኛ ነው፣ አማርኛ ቀሪውን ከ11 እስከ 18 በመቶ የሚሆነውን ይይዛል (ዙዋግ, 2020: ፀጋዬ እና አጥናፉ, 2016)። የዊኪፔዲያ ገፆች በሀገሪቱ አምስት የመንግስት የስራ ቋንቋዎች መኖራቸውን መጥቀስ ተገቢ ነው ምንም እንኳን አማርኛ በመድረኩ ላይ ከፍተኛ ታይነት ያለው ቢሆንም።

በመጨረሻም ወደ ማህበራዊ ሚዲያ ስንመጣ ፌስቡክ - በአገሪቱ ውስጥ በጣም ታዋቂው የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ - የተጠቃሚ በይነ-ገጽን ለማሰስ ወይም ለመመልከት የትርጉም ድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል ፣ነገር ግን የማህበረሰብ መመሪያዎቹ (Community standards) በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፊደል ወይም ቋንቋ አልተፃፉም እንዲሁም አይገኙም (አያሌው 2021)።

**Daniel Yacob**
@ethiopic

Nice to see an #Amharic keyboard arrive with iOS 15. It's fairly normal, with a few clever choices.  Offering non-Amharic letters may cause some confusion, slow typing, and lead to more spelling errors. Better to support these letters under additional keyboards. But it's a start!




4:12 AM · Sep 22, 2021 · Twitter Web App

**Daniel Yacob**
@ethiopic

To clarify the hazard of the approach, it is analogous to adding French, German, Czech, etc. letters to an English language keyboard.

4:39 AM · Sep 22, 2021 · Twitter Web App

ልክ እንደሌሎች የአህጉሪቱ ቦታዎች የሞባይል ስልክ በኢትዮጵያም ተጀምሯል። ይህም ሆኖ፣ የሞባይል ምዝገባዎች እና ብዙ የኢንተርኔት ዝርጋታዎች በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ሲሆኑ፣ አብዛኛው ኢትዮጵያውያን የሞባይል ስልክ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት አልነበራቸውም (Kemp, 2021; World Bank, 2020) ። ይህም ሆኖ ኢትዮጵያውያን የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙባቸውና የሚጠቀሙባቸው ቀዳሚ መንገዶች ሞባይል ስልኮች ናቸው። በኮርናይ እና ሌሎች (2017) የተሻሻለ ምዘና ስኬል በመጠቀም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በበይነመረብ ላይ መኖራቸውን በሚመለከት በተደረገው የዙዋግ (2020) ትንታኔ መሰረት አማርኛ በዲጂታል ድጋፍ፣ አጠቃቀም እና ጠቃሚነት ጎራዎች የበለጸገ ባይሆንም በዲጂታል መድረኮች ላይ ወሳኝ ተደርጎ ይወሰድ ነበር።

ትንታኔው እንደሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋ በዊኪፔዲያ (Wikipedia) እና ትዊተር ይዘቶች ላይ ከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚነት አለው። የሶማሊያ ብሔራዊ ቋንቋ የሆነው ሶማሊኛ የላቲን ፊደልን የሚጠቀም ሲሆን ልክ እንደ አማርኛ በተመሳሳይ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ደረጃ ላይ ይገኛል። የተቀሩት የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች በዲጂታል አጠቃቀሞች ማለትም በትርጉም ፣ የቋንቋ ተደራሽነት ፣ የፍለጋ አገልግሎቶች ወዘተ ባሉ ዲጂታል አጠቃቀሞች ጥሩ መጠን ካለውና ዲጂታል ድጋፍ ከሚያገኘው ከትግርኛ ቋንቋ በቀር በይነመረብ ላይ ያላቸው ተግባራዊ አገልግሎት አነስተኛ ነው። ከአመለካከት አንፃር ደግሞ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ቋንቋዎች የበይነ-መረብ ይዘቶችን በከፍተኛ ደረጃ እየፈጠሩ ባሉበት ወቅት፣ የይዘት አጠቃቀሙ ግን አሁንም ወደ እንግሊዝኛ ያዘነብላል። በኮል(2014) መሰረት እንግሊዝኛ ቋንቋን የሚጠቀሙ ኦትዮጵያውያን የአማርኛ ዊኪፔዲያን በጎበኙ ቁጥር 57 ጊዜ እንግሊዘኛ ዊኪፔዲያን ጎብኝተዋል። ዛውግ (2017) በፌስቡክ ልጥፍ አስተያየቶች ላይ ባደረገው ትንተና ፌስቡክ የአማርኛ ግዕዝ ፊደላት ቢኖረውም የተፃፉት ከ50% በላይ አስተያየቶች ግን በላቲን ፊደል መሆናቸውን ተመልክቷል።

# ታንዛኒያ

ታንዛኒያ ከአፍሪካ በጣም የተለያዩ ቋንቋዎች ከሚነገሩባቸው ሀገራት አንዷ ናት። በአገሪቱ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉ ከ 99 እስከ 150 የሚደርሱ ቋንቋዎች አሉ። ሱዋሂሊ እና እንግሊዝኛ የሀገሪቱ ይፋዊ ዕውቅና ያገኙ ቋንቋዎች ሲሆኑ ሱዋሂሊ የሀገሪቱ ቋንቋ በመባል ይታወቃል። በዘዬ እና በአነጋገር የተለያዩ ቢሆኑም ፣ሱዋሂሊ በምሥራቅ አፍሪካ ወደ 200 ሚሊዮን ገደማ ተናጋሪዎች አሉት። (Siminyu et al., 2022) በተጨማሪም አብዛኛዎቹ ታንዛናውያን ይናገሩበታል እንዲሁም ይረዱታል። ልክ እንደሌላው የአህጉሪቷ ክፍሎች፣ በታንዛንያ ያለው ቀጣይነት ያለው የቋንቋ የበላይነት ተለዋዋጭነት በቅኝ ግዛት ታሪኳ እና ከነፃነት በኋላ እውን ከሆኑት ምኞቶች ጋር የተቆራኘ ነው።

እንግሊዝኛ በታንዛኒያ የቋንቋ ታሪክ ውስጥ በአንጻራዊ ሁኔታ የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው። በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አስተዳደር ወቅት በሃያኛው ክፍለ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። በ (ብዌንጌ, 2012) መሠረት የዚህ ቋንቋ ግልጋሎት የከፍተኛ-ደረጃ አስተዳደር እና የአካዳሚክ ዘርፍ ቋንቋ በሚል ተለይቶ ነበር። በተጨማሪም የቋንቋው ግልጋሎት ለባለሙያ ሠራተኞች እንዲውል የተለየ ሲሆን ይህም ቋንቋውን ከፍ ወዳለ ዕድል የሚያደርስ ተደርጎ እንዲቆጠር ምክንያት ሆኗል። ይህ በእንግሊዝኛ አጠቃቀም እና ዋጋ ዙሪያ የሰዎችን እምነት እንደ ማህበራዊ ሀብት ብቻ ሳይሆን ከየራሳቸው የአገሬው ተወላጅ ቋንቋዎች ጋር በማያያዝ መቅረፁ የማይቀር ነው። ነገር ግን ሱዋሂሊ በአገሪቱ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ቆይቷል። በ ሁዊትሊ, (1969) መሠረት በጥቂቱ ለመነገሩ ማስረጃ ከ 10 ኛው ክፍለዘመን በፊት ጀምሮ ሊገኝ ይችላል፣የተስፋፋውም በ 19ኛው ክፍለ ዘመን በንግድ እና በትምህርት በኩል እንደሆነ ይገለጻል (ሩባግሙያ,1990); በዚህ ጊዜ መገባደጃ ላይ ጀርመን የታንዛኒያ አስተዳዳሪ ሆነች። በዚህ የአገዛዝ ዘመን ጅማሮ ስዋሂሊ የሀገሪቷ ቋንቋ ሆኖ ተጠብቆ የቆየ ሲሆን በአስተዳደራዊ ሥርዓቶች ውስጥም እንደ ይፋዊ የመግባቢያ ቋንቋ ሆኖ ቆይቷል (ዊትሊ, 1969)። ሆኖም ጀርመንኛ የሀገሪቱ ይፋዊ ቋንቋና አስፈላጊ ዕድሎችን ለማግኘት የሚጠቀሙበት ዋነኛ ቋንቋ መሆኑን እስጠብቆ ቆይቷል። ከዚህ በኋላ በአንፃራዊነት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንግሊዝ እንግሊዝኛ ቋንቋን የሀገሪቱ ይፋዊ ቋንቋ አደረገች። እንግሊዞች የተለየ ዝንባሌ ስለነበራቸው ሱዋሂሊ ዋነኛ ቋንቋ መሆኑን በማረጋገጥ ረገድ ንቁ ነበሩ። በምስራቅ አፍሪካ-ክልላዊ ቋንቋ ኮሚቴ አማካኝነት የአንግሊዝ ቅኝ ግዛት አስተዳደር በታንዛኒያ እና ምስራቅ አፍሪካ የሱዋሂሊ ቋንቋ እንዲስፋፋ አድርጓ (ሲሚንዩ እና ሌሎች., 2022; ሚንሶኮ,1991)። ለዝቅተኛ የአስተዳደር እርከን እና ለመሰረታዊ ትምህርት መገልገያ ቋንቋ ሆኖ ቆይቷል። ሱዋሂሊ በታሪክ ለ 'ህብረ ብሄራዊ አንድነት እና ውህደት'' መሳሪያ ተደርጎ እንደመቆጠሩ መጠን፣ በብሔራዊ ንቅናቄዎች ውስጥ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። በተለይም ነፃነትን እውን በማድረግ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫውቱት ፓርቲዎች (የታንጋኒካ አፍሪካ ብሔራዊ ህብረት እና የታንጋኒካ አፍሪካ ማህበር) ሱዋሂሊን ለፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ተጠቅመዋል።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ትምህርት ፣ለከፍተኛ አስተዳደር እርከን እና ለልሂቃን መገልገያነት ተለይቶ መዋሉ ሱዋሂሊ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ቋንቋ ተደርጎ እንዲታይ ምክንያት ሆኗል (Bwenge,2012) ። የታንዛኒያ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር እና ከነፃነት በ|ላ ፕሬዝዳንት የሆኑት ጁሊየስ ኒዬሬ ሱዋሂሊን ብሔራዊ ቋንቋ አድርገው ያወጁት በዚህ መነሻ ምክንያት ነበር። በዚህ የቋንቋ ፖሊሲ መሠረት ሱዋሂሊ የመጀመሪያ ደረጃና የጎልማሶች ትምህርት ቋንቋ ሆኖ ተጀመረ፤ ይህም ግልጋሎቱን

ወደ ከፍተኛ ደረጃዎች ለማስፋት ያለመ ነው (ማዝሩል እና ሌሎች፣ 1998)።

በመሠረቱ ስዋሂሊን ፖለቲካዊ መልክ ማስያዝ (ፖለቲሳይዜሽን) ወይም 'ስዋሂላይዜሽን' ፕሮጀክት በሦስት ዋና ዋና ሀሳቦች የተደገፈ ነበር (1) ብሔራዊ አንድነት ለማጎልበት (2) የጎሳ ቅስቃሴዎችን ለማስቀረት፣ እና (3) ለአንድ ጎሳ ያልተለየ የጋራ ቋንቋን በመጠቀም የእኩል ዕድል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ነው። ይህ ሂደት በጊዜው በትምህርት ሚኒስቴር እና በማህበረሰብ ልማት እና ባህል ሚኒስቴር ስር ባሉ በርካታ የቋንቋ ፖሊሲዎች እንዲሁም ቁልፍ እንቅስቃሴዎች አማካይነት ተመቻችቷል። ለምሳሌ የስዋሂሊ ቋንቋ ደረጃ አሰጣጥ፣ ዕድገት እና ስርጭትን የማስተባበር ኃላፊነት የተሰጠው ብሔራዊ የስዋሂሊ ምክር ቤት (BAKITA) እና በዳሬሰላም ዩኒቨርሲቲ የስዋህሊ ጥናቶች ተቋም (TATAKI) የዚህ እንቅስቃሴ ግንባር ቀደም ነበሩ (ብዌንጅ ,2012)። የስዋሂሊ አጠቃቀምን ለማስፋትና ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶች አሉታዊ ምላሽ ገጥሟቸዋል። በስዋሂሊ ለሁለተኛ እና ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ጠቃሚነት ላይ ለተነሳው ከፍተኛ የህዝብ ጥያቄ ምላሽ መንግሥት እንግሊዝኛን የማስተማሪያ ቋንቋ አድርጎ ነበር። በ ባቲቦ (1995) መሰረት በዚህ ጊዜ የእንግሊዝኛ ሚና እና ክብር በሚታይ መልኩ ቀንሷል፣ ይህም የሆነው ስዋሂሊ ፈጣን እና አዎንታዊ የሚባል ዕድገትን በማሳየቱ ነው። ይህም ሆኖ በአሁኑ ጊዜ እንግሊዝኛ የግል ትምህርት ስርዓቱን ተቆጣጥሯል፣ ትምህርት ቤቶችም ከበርቴ ቤተሰቦችን ለመሳብ እንደ የግብይት መሣሪያ እየተጠቀሙበት ነው። በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የዕድገት፣ የተደራሽነት እና ዕድልን የማግኛ ቋንቋ ተደርጎ መታየቱን ቀጥሏል። የሆነ ሆኖ እንግሊዝኛ በተለምዶ ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልሂቃን የተለየ አናሳ ቋንቋ ነው። እ.ኤ.አ. በ 2015 ዓ.ም የተጀመረው አዲሱ የትምህርት እና የሥልጠና ፖሊሲ ስዋሂሊን በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሀገሪቱ የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን አድርጎ አፅድkል (ዩኒሴፍ, 2017)።

ስዋሂሊ ሌሎች የሀገሪቱን ቋንቋዎችን መገዳደር በመቻል በአህጉሪቱ ብቸኛው ቋንቋ መሆኑ የበላይነቱን ለየት ያደርገዋል (ሮዜንዳል 2016)። በተለይ በታንዛኒያ አጠቃቀሙ እና ዕድገቱ የተመሰረተው ሌሎች የማህበረሰብ ቋንቋዎች ላይ የበላይ በመሆን ነው። ለምሳሌ (ማፑንዳ እና ጊብሰን, 2022) ባገኘዉ ማስረጃ መሰረት ዕድገቱ እና የበላይነቱ የተመሰረተዉ በሌሎች ሀገር በቀል ቋንቋዎች ላይ በተለይም በወጣቶች መካከል አድልዎ በማድረግ ነው። ይህ በምርጫዎች ብቻ የተገደበ አልነበረም፣ ይልቁንም ማፑንዳ (2013) እና ሮዜንዳል እና ማፑንዳ (2014) በሰዎች ባህላዊ ማንነት እና እሴቶች ላይ ትልቅ አንድምታ አግኝተዋል ለምሳሌ ሱዋሂሊን ከሌሎች የሀገሪቱ ቋንቋ አንፃር የበላይ ወይም የህብረተሰቡ ቋንቋዎችን ከስዋሂሊ አናሳ አድርጎ መቁጠር ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳደሩን አስተውለዋል። ነገር ግን ሱዋሂሊ እንደ ዋና ቋንቋ በማይነገርባቸው ወይም ሌሎች የማህበረሰብ ቋንቋዎች በሚነገሩባቸው ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ክህሎታቸውን ማሳደግ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖችን እንዳሳደረባቸው ይጠቁማሉ። (ማፑንዳ እና ጊብሰን, 2022) በታንዛኒያ የጥናት ክልላቸው ዉስጥ ባገኙት ግኝት ከሱዋሂሊ ውጪ ያሉ ቋንቋዎች በተስፋፉባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚወድቁ (የሚደግሙ) ተማሪዎች በተደጋጋሚ ተስተውለዋል። በተመሳሳይም በታንዛኒያ ውስጥ የትምህርት ሁኔታን በሚገመግሙበት ጊዜ በ (ኡዌዞ ታንዛኒያ, 2017) ግኝት መሠረት ስዋሂሊን እና በቀጣዮቹ ዓመታት ደግሞ እንግሊዝኛን በብቸኝነት ለትምህርት ጥቅም ላይ

ማዋላቸው በመላ አገሪቱ ባሉ ተማሪዎች የስኬት ደረጃ ላይ አንድምታ እንደነበረው አረጋግጠዋል። በመጨረሻም እኩልነትን ያረጋገጠ ስኬት መገኘቱን የሚጠቁም ማስረጃ መኖሩ አጠያያቂ ነው። ስዋሂሊ በአገሪቱ ውስጥ የተለያየ ባህል ላላቸው ግለሰቦች እኩል ዕድልን የማረጋገጥ ችሎታው ላይ በቂ ማስረጃ የለም።

ልክ እንደሌሎች አፍሪካውያን ቋንቋዎች ስዋሂሊም፣ በታሪክ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር ተያያዥ ግንኙነት አለው (ሌጌሬ፣ 2006) ። በቅኝ ግዛት ወቅት የአገር ውስጥ ቋንቋ ይዘቶችን ከወደ አገር ውስጥ ወደሚገቡ ቴክኖሎጂዎች (በዋናነት ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲሰሩ ከሚጠበቅባቸው መሳሪያዎች) ጋር ለማዋሃድ የተደረገ ሙከራ አልነበረም። በዚህ ምትክ፣ የስዋሂሊ ተናጋሪዎች የቋንቋ መበደርን ተለማመደዋል፣ ይህም አሰራር በክልሉ ውስጥ በአይሲቲ ቋንቋ ውስጥ ተቀርጾ ቆይቷል። ይህም በአካባቢውም በአገር ውስጥ ቋንቋ አዳዲስ ቃላትን ለማውጣት እና ለመቀበል የተቀናጀ ጥረት ተደርጓል (ምዚራይ, 2019፣ ሌጌሬ, 2006፣ ማዙሪ እና ማዙሪ, 1995) ። በሰፊው ጥቅም ላይ ቢውልም ፣ ትልቅ የጽሑፍ እና የንግግር መረጃ ማከማቻ ከመኖሩ በተጨማሪ ስዋሂሊ 'አናሳ' ቋንቋ ተደርጎ እንደተቆጠረ ነው (ሺካሊ እና ሞክሆሲ, 2020) ። የስዋሂሊ ወደ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ማካተት በእጅጉ ተሻሽሏል። የድረ-ገጽ እና የበይነመረብ ይዘት አቅርቦት ከመጨመር ባሻገር በኪስዋሂሊ ውስጥ የሚሰሩ ተመጣጣኝ ቴክኖሎጂዎች ወይም መሳሪያዎች ተደራሽነት በተመሳሳይ መልኩ መሳብ ችለዋል (ሃልቮርሰን, 2012) ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ለቋንቋው የሚደረግ ዲጂታል ድጋፍ እየጨመረ መጥቷል። ማይክሮሶፍት እና ሊኑክስ በክልሉ ውስጥ ቴክኖሎጂን አካባቢያዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ቀዳሚዎች ነበሩ (ዋንዴራ, 2014) ። ከ2000 ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ሁለቱም ኩባንያዎች የኮምፒውተራቸውን ሶፍትዌር በስዋሂሊ ስሪቶችን አስጀምረዋል። ስዋሂሊን በአይሲቲ ውስጥ ለማካተት ከሚደረጉ ጥረቶች መካከል የጎግል ስዊት ምርቶች መገኘት፣ የፅሁፍ ከንግግር (TTS) ስርዓቶችን ማዘጋጀት፣ እንደ ሳላማ ያሉ የተለያዩ የማሽን ተርጓሚዎችን ማስተዋወቅ እና የሞዚላ ፋውንዴሽን ለጋራ የመረጃ ቋት እና በቋንቋው ለጋራ ድምጽ የውሂብ (ዳታ) ስብስብ ለመገንባት እያደረገ ያለውን ጥረት ሁሉ ያጠቃልላል (ካማዉ, 2007፡ ሲሚኒዩ ኢቲ ኤል., 2022)። ወደ ስዋሂሊ እየተተረጎሙ ካሉ በርካታ አፕሊኬሽኖች በተጨማሪም M-PESA - በ221 ከ50 ሚሊዮን በላይ ተጠቃሚዎች ያሉት የአፍሪካ በጣም የተሳካ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት መድረክ (ኦሉወሌ, 2021) በስዋሂሊ ውስጥ የቋንቋ ምርጫ አለው ይህም በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለውን ህዝብ ያስጠቀማል ተብሎ ይታመናል (ዋንዴራ, 2014) ። ይሁን እንጂ የስዋሂሊ ተናጋሪዎች አካባቢያዊ ከሆነው የበይነ-መረብ አገልግሎት ሙሉ ጥቅማጥቅሞችን እንዳያገኙ ከሚያደናቅፉ ቁልፍ ጉዳዮች አንጻር የዲጂታል ድጋፍ አልተስፋፋም። አብዛኛው የኪስዋሂሊ የትርጉም እንቅስቃሴ በቋንቋ ላይ ያተኮረ ሲሆን ሌሎች የትርጉም ገጽታዎች ላይ ግን አናሳ ትኩረት ነው ያለው። ይህም እንደ የተሳሳቱ ትርጉሞች፣ ከመጠን በላይ በራስ እርማት እና ለመጠቀም አስቸጋሪ የሆኑ የድምጽ አገልግሎቶችን የመሳሰሉ ተግዳሮቶችን አስከትሏል (ቡሊቪያ, 2017) ። በወቅቱ በስፋት ከተሰራጨው ዜና ተቃራኒ በሆነ መንገድ እና በማህበራዊ ድህረ-ገፆች እራሱ እንደገለጸው, ስዋሂሊ አሁንም የተተረጎመ የመግብር ጽሑፍ ካለባቸው በትዊተር ሰላሳ አራት የሚደገፉ ቋንቋዎች አንዱ አይደለም። በናሙናቸው ውስጥ ያሉ የM-Pesa ተጠቃሚዎች ከኪስዋሂሊ በተቃራኒ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ምርጫን መጠቀም የመምረጣቸውን ጉዳይንም ዋንዴራ (2014) ማንሳቱን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። ምንም እንኳን ስዋሂሊ የበለጠ ምቹ የሆነበት ቋንቋ ቢሆንም፣

የማያውቁት የቃላት አጠቃቀሞች እና ምርጫው ልክ እንደ እንግሊዝኛ እትም እንከን የለሽ አለመሆኑ በምክንያትነት ተጠቅሰዋል። ይህ አካባቢያዊ የማድረግ ቴክኖሎጂ እና በይነመረብን ለየት ባለ መልኩ በእንግሊዘኛ አውድ መተርጎምን መነሻ በማድረግ ዙርያ ያሉ ፈተናዎችን ይወክላል።

በታንዛኒያ የሞባይል ስልክ የሀገሪቱን ሩቅ ክልሎች እንኳን ሳይቀር በስፋት መድረስ ችሏል። ከሞባይል መሳሪያዎች ተደራሽት አንፃር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ታንዛናውያን በይነ-መረብን በዋነኝነት የሚጠቀሙበት የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው አካል ሆኗል። በተጨማሪም የሞባይል መሣሪያዎች ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አካባቢያዊ ይዘት ያላቸው የተለያዩ የበይነመረብ ይዘቶችን ተደራሽ ለማድረግ አስችለዋል። ታንዛኒያውያን ከማህበራዊ ሚዲያ ባሻገር በብዙ ምክንያቶች የሞባይል መሳሪያዎችን መጠቀምን ምርጫቸው ያደርጋሉ። የፋይናንስ ግንኙነቶችን ለማካሄድ የሞባይል መሳሪያዎቸች በስፋት ጥቅም ላይ ይውላሉ (እንቶኒ እና ሙታሌምዋ፣ 2014)። በመላ ሀገሪቱ ያሉ ተማሪዎች የትምህርት ልምዶቻቸውን ለማሳደግ የሞባይል ስልክን እንደ መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙታል። (ሙዋፔሌ እና ሩድት፣2016። ኪቦና እና ሩጊና፣ 2015። ካፊውሊሎ፣2014)

የአገሪቷ አንድ ሚሊዮን የጎዳና ነጋዴዎች ንግዶቻቸውን ለማካሄድ እነዚህን መሳሪያዎች ይጠቀማሉ። (ሩማኒካ እና ሌሎች ፣ 2019) ገቢ የሚያመነጩበትን መንገድ ለማሳለጥ የሞባይል መሣሪያዎችን የሚጠቀሙ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል (ማንዩሬሬ፣2021)። በተጨማሪም ሬስተር-ኖን (2021) ታንዛናውያን የስዋሂሊ ልብ ወለድን ተደራሽነት ለማሳደግ በይነመረብን እንዴት እንደተጠቀሙ አስተውለዋል። ምንም እንኳን እነዚህን ግንኙነቶች መሠረት ያደረጉ ቴክኖሎጂዎች በእንግሊዝኛ በብዛት የሚገኙ ቢሆኑም ፣አሁንም ድረስ በስፋት የሚነገረው ቋንቋ ስዋሂሊ ነው። ነገር ግን ማፑንዳ እና ሮዜንዳል (2021) ይህ ከቴክኖሎጂ ጋር ያለው ትስስር በተለይም በወጣቱ በኩል የእንግሊዝኛን መስፋፋት እና ተቀባይነቱን እንደጨመረ ልብ ብለዋል።

እነዚህን ቴክኖሎጂዎች የመጠቀም አማራጭ በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች በሚገኙበት ጊዜ እንኳን ይህ ተስተውሏል። በዳረ ሰላም ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ላይ በተደረገ ጥናት ሃልቭሮሴን, (2012) ሱዋሂሊ ከመገናኛና መረጃ ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖረውም አንዳንድ ተማሪዎች ቋንቋው |ላቀር፣ ጠባብ እና አካዳሚያዊ ያልሆነ አድርገው በመቁጠር ለቴክኖሎጂ ተገቢ ቋንቋ አይደለም ብለው እንደሚያስቡ አጥንተዋል። ማላንግዋ (2019) እንዳስረዳው አንዳንድ ጊዜ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በእንግሊዝኛ የታተመውን መረጃ ተደራሽነት ለመጨመር ተጠቃሚዎች ሆን ብለው የተለያየ ቋንቋ ይጠቀማሉ። በብዙሀኑ እንግሊዝኛ ወደተሻለ ቦታ የሚያደርስ ቋንቋ እንደሆነ ይታሰባል። ዓለም ወደ አንድ መንደር እየመጣችበት ያለውን (የግሎባላይዜሽን) ፍጥነት ከግምት በማስገባት ታንዛናውያን፣ በዓለም ዙሪያ እንዳሉት ሁሉ፣ ከዕድሎች እና ከማህበራዊ ዕድገት እንዳይገለሉ በመፍራት እንግሊዝኛ ቋንቋን ለመተው ፈቃደኛ አይደሉም። በተጨማሪም በጣም ብዙ መረጃዎች ተደራሽነታቸው በእንግሊዝኛ ብቻ እንደሆነ ቀጥሏል።

# ኡጋንዳ

በኡጋንዳ ቢያንስ 41 ቋንቋዎች ቢኖሩም፣ አሁን ያሉት የኡጋንዳ ብሔራዊ ቋንቋዎች እንግሊዝኛ እና ስዋሂሊ ናቸው። እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ ስዋሂሊ ሲሶ በሚሆኑት የኡጋንዳ ዜጎች የሚነገር የነበረ ሲሆን የአስተዳደር፣ የንግድ እና የትምህርት መጠቀሚያ ቋንቋ ነበር። ምንም ያህል የማዕከላዊው ክልል አጠቃቀሙን እንደ ማስፈራሪያ ቢቆጥረውም እንኳን የኢዲ አሚን ዳዳ አምባገነን አገዛዝ የስዋሂሊ አጠቃቀም እንዲጨምር አድርጓል። አሉታዊ ትርጉም ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም እ.ኤ.አ በመስከረም 2019 ላይ የኡጋንዳ መንግስት የብሔራዊ የስዋሂሊ ምክር ቤት መመስረትን አፀደቀ። የኡጋንዳ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 6 (2)ም "ፓርላማው በሕጉ በሚያዘው ጊዜ በኡጋንዳ ውስጥ ሁለተኛው ኦፊሴላዊ ቋንቋ ስዋሂሊ ይሆናል" ይላል።

እ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ እንግሊዘኛ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት 5ኛና ከዛ በላይ ላሉት ክፍሎች የመማሪያ ቋንቋ ሆነ። ስዋሂሊ እንደ "ኡጋንዳውያንን አንድ ለማድረግ እና ፈጣን ማህበራዊ ልማትን ለማጎልበት የላቀ አቅም ያለው ቋንቋ" በገጠር እና በከተማ ባሉ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ4- 7ኛ ክፍል ተማሪዎች አስገዳጅ ሆኖ እንዲሰጥ ተደርጓል። ይህ በኋላ በ2007 ዓ.ም ወደተቋቋመው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ፖሊሲ ተለወጠ።በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተካተቱት ቀዳሚ ቋንቋዎች ሉጋንዳ፣ ሉኦ ሩንያኪታራ/ሩኒዮሮ-ሩቶሮ እና ሩንያንኮሬ-ሩኪጋ አቴሶ/አካራሞጀንግ እና ሉግባራ፣ በኡጋንዳ ውስጥ ካሉ ሌሎች የቋንቋ ቤተሰቦች ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ተመስርተው ነበር። በዚህ አዲስ ህግ መሰረት በመጀመሪያዎቹ ሶስት አመታት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ቋንቋ እንዲማሩ ተደርጓል። እንግሊዝኛም ተካቷል ግን ራሱን እንደቻለ የትምህርት ርዕሰ-ጉዳይ ነበር። በአራተኛው ዓመት ሥርዓተ ትምህርቱ እንግሊዘኛን እንደ ዋነኞቹ የማስተማሪያ ቋንቋዎች ወደ አንዱ እንዲያድግ አድርጓል። በአምስተኛው ዓመት ደግሞ እንግሊዘኛ ብቸኛው የማስተማሪያ ቋንቋ ሆነ። ይህ እንግሊዝኛን እንደ የማስተማሪያ ቋንቋቸው ብቻ ከሚጠቀሙት በኡጋንዳ ከሚገኙት የግል እና አለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች ጋር በቀጥታ የሚቃረን ነው።

ሉጋንዳ በሀገሪቱ ውስጥ በብዛት የሚነገር የአገሬው ተወላጅ ቋንቋ ነው፣ነገር ግን አሁንም የተናጋሪ ብልጫ የለውም። ይህ ቋንቋ 16.7% የኡጋንዳ ህዝብ በሚይዘው በባጋንዳ የሚነገር ነው። የሉጋንዳ ተናጋሪዎች በደቡብ ምስራቅ (በቪክቶሪያ ሀይቅ ዳርቻዎች) እና በሰሜን (ከኪዮጋ ሀይቅ ዳርቻ) በማዕከላዊ ዩጋንዳ ክልሎች ይኖራሉ። ሉጋንዳ ምንም አይነት የይፋዊ ዕውቅናን ባያገኝም፣ ካምፓላ የሀገሪቱ የመንግስት እና የንግድ መቀመጫ በመሆኗ ሉጋንዳ በመላ ሀገሪቱ የንግድ እና የግለሰቦችን ስራ መግባቢያ እንዲቆጣጠር አድርጎታል። በሌላ በኩል አራት ተጨማሪ የተሰየሙ የክልል ቋንቋዎች አሉ፡ ሩንያኪታራ ለምእራብ ኡጋንዳ፣ ሉኦ ለሰሜን ኡጋንዳ እና አቴሶ እና ንጋካሪሞጀንግ ለሰሜን-ምስራቅ ኡጋንዳ ናቸው።

እንደሌላው ሀገር ሁሉ ኡጋንዳውያን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ወደ እንግሊዘኛ ቀይረዋል። ለምሳሌ፣ በባንቱ ቤተሰብ ስር ያሉ ቋንቋዎች ብቻቸውን የሚሰሙ ተነባቢዎች የላቸውም። ተነባቢ ባለበት፣ ተጓዳኝ አናባቢ መኖር አለበት። እንግሊዝኛ በኡጋንዳ ለልሂቃን ዋና ቋንቋ ሆኖ ይቀጥላል፣ እና ብዙ ጊዜ የተለያዩ ቋንቋዎች ባላቸው ክልሎች መካከል እንደ አንድነት ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል፣ በተለይም በበይነ መረብ ላይ። በተጨማሪም፣ እንግሊዝኛ እንደ "ማረጋገጫ" ቋንቋ ነው የሚታየው፣ በቅኝ ግዛት ውርስ ምክንያት፣ ብዙ ጊዜ የበለጠ ትክክለኛ ወይም "ባለዕውቀት" ተብሎ የሚታሰብ ነው። ትክክለኛውን ስም እንደ ግስ

በመጠቀም የኢንግሊዝኛን አስፈላጊነት ለማሳየት የሚጠቀሙበት አሉ። ይህን ለማድረግ ገንዘብ ያላቸው ሀብታም፣ ከፍተኛ እና መካከለኛ ደረጃ ያላቸው ዩጋንዳውያን እንግሊዝኛን እንደ ሙያዊ እና የግል መሳሪያ በመጠቀም እውቅና እና ዝናን ለማግኘት ይጠቀሙበታል። በሉጋንዳ ወይም በሌሎች የአካባቢ ቋንቋዎች ምትክ እንግሊዘኛ ከዕድል፣ ከትምህርት እና ከሀብት ጋር የተያያዘ ነው። ይልቁንም ሉጋንዳ ከሙዚቃ፣ ንግድ እና ሃይማኖታዊ ሕይወት ጋር የተቆራኘ ነው (ሴታንዳ እና ናካይዛ፣ 2015)።

በኡጋንዳ ውስጥ ስለ እንግሊዘኛ የበላይነት የሚገልጹ ጽሑፎች እጥረት እያለ፣ እንግሊዘኛ፣ እንደ ቅኝ ገዥ ቋንቋ፣ እንደ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሣሪያ እንዴት እንደሠራ ለመረዳት የናይጄሪያን ምሳሌ ልንጠቀም እንችላለን። አዲመጂ (2004) የእንግሊዘኛን አጠቃቀም እንደ ሀገራዊ ልማት አካል አድርጎ ተንትኗል፣ በዚህ ውስጥ ከ500 በላይ የአገሬው ተወላጅ ቋንቋዎች በሚነገሩበት አገር ውስጥ እንደ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል። ምንም እንኳን የእንግሊዘኛ ቀጣይነት ያለው አጠቃቀም ቅኝ ግዛትን የሚቀጥል ቢሆንም፣ እንግሊዘኛ የሚይዘውን የተሻለ ቦታ መያዝ የሚችል ሌላ አማራጭ አገር በቀል ቋንቋ እንደሌለ ያምናል። በኡጋንዳ እና በናይጄሪያ የእንግሊዝኛ ወይም ሌሎች የምዕራባውያን ቋንቋዎች በበበይነ መረብ የበላይነት መኖር በአፍሪካ ዲጂታል መድረክ ውስጥ የቋንቋ ልዩነት እንዳይኖር ያደርጋል። የአፍሪካ ሀገራት በቋንቋ ረገድ በአውሮፓ እና በምዕራብ ላይ ጥገኛ ናቸው (ኦቦንዶ, 2007) ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ሀገር-በቀል ቋንቋዎች ተመሳሳይ የመተግበሪያ መንገዶች የላቸውም። እንግሊዘኛ አቀላጥፈው መናገር የማይችሉ ወይም ጨርሶ የማይናገሩ የመናገር መብትን ለመጠየቅ ተግዳሮት ይገጥማቸዋል። (ኖርተን፣ 2015)።

ኡጋንዳ ውስጥ፣ አብዛኛዎቹ ብሔራዊ ሚዲያዎች በእንግሊዝኛ እና በሉጋንዳ ይዘቶችን ያዘጋጃሉ፣ አልፎ አልፎም በስዋሂሊ ይታተማሉ። ምንም እንኳን የክልል የሀገር ውስጥ ህትመቶች ቢኖሩም እንኳን እንደ ካምፓላ ላይ የተመሠረቱ ሕትመቶች ብሔራዊ ጥቅምም ሆነ መገለጫ የላቸውም። ኒው ቪዥን በመባል የሚታወቀው ጋዜጣ በየቀኑ የሚታተመውን የሉጋንዳ ጋዜጣን ጨምሮ ቡኬዴ፣ እንዲሁም ኦሩሙሪ፣ ኢቶፕ እና ሩፒኒ የሚባሉትን ሳምንታዊ ጋዜጦችን ያትማል። አብዛኛው የቴሌቭዥን ፕሮግራም በእንግሊዝኛ ሲሆን አብዛኛው የሬዲዮ ፕሮግራም ደግሞ በሉጋንዳ እና በእንግሊዘኛ ይከፋፈላል። ነገር ግን፣ ትንንሽ የአገሬው ተወላጅ ቋንቋዎች “ለንግድ የማይጠቅሙ ፕሮግራሚንግ” ተብለው በመፈረጃቸው ምክንያት ትላልቅ የቋንቋ ቋቶች (እንደ ሉጋንዳ ያሉ) በፕሮግራም እና በይዘት ውስጥ አንድ ወጥነት አላቸው (ቺቢታ, 2016) ። በዚህም ምክንያት አብዛኛው የሀገር ውስጥ ይዘቶች ወይ አልተዘጋጁም ወይ ደግሞ የአካባቢ ጉዳዮችን ለተመልካቾች ተደራሽ በሆነ ቋንቋ አያቀርቡም። ሉጋንዳ፡ በኡጋንዳ የሚዲያ ስፔስ ውስጥ በአንፃራዊነት የተለመደ እንደሆነ የሚታወቀው ቋንቋ እንኳን በሶፍትዌር፣ በኮድ እና በፕሮጀክት ልማት ጥሩ አይደለም (ናቤንዴ ኢቴ ኤኤል., 2021)

በዚህም ናቤን እና ባልደረቦቹ (2021) ኮቪድ-19ን የተመለከተ የተሳሳተ መረጃ በሉጋንዳ፣ እንግሊዝኛ እና ድብልቅ ሉጋንዳ-እንግሊዘኛ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ለመረዳት ሉጋንዳን ያካተተውን የመጀመሪያውን የተሳሳተ መረጃ ስብስብ

ተንትነዋል። ቡድኑ በኮድ የተቀላቀለው ሉጋንዳ-እንግሊዘኛ መልዕክት የተሳሳተ መረጃ ይይዝ እንደሆነ ወይም እንደሌለበት ለመለየት በእነዚህ የውሂብ(ዳታ) ስብስቦች ላይ የማሽን-መማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርጓል (ናበንዴ እና ሌሎች., 2021) ። በማጠቃላያቸውም፣ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በፍጥነት የሚሰራጩ አደገኛ የሆኑ የተሳሳቱ መረጃዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማግኘት ሶፍትዌሩ ገና አልተሰራም።

በተጨማሪም፣ በተለይም አክቲቪስቶች ወይም የዕለት ተዕለት ተጠቃሚዎች በበይነመረብ ላይ ሀሳባቸውን ለመግለጽ የአካባቢያቸውን ቋንቋ በሚጠቀሙበት ጊዜ የዲጂታል ደህንነት ብዙ ጊዜ አደጋ ላይ ይወድቃል። እየቀጠለ ባለው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በዋትስአፕ ቡድኖች፣ ፌስቡክ እና ትዊተር ላይ የተሳሳተ መረጃ ይሰራጫል፣ ስለ ክትባቶች እና ህክምናዎችም ፍፁም ውሸት የሆኑ የተሳሳቱ መረጃዎች አሉ። በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በፍጥነት የሚሰራጩ አደገኛ የሆኑ የተሳሳቱ መረጃዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመያዝ ሶፍትዌሩ ገና እንዳልተሰራ በማሳየት አጠቃለዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የኡጋንዳ አክቲቪስቶች በየትኛውም ቋንቋ በትዊት፣ ዋትስአፕ አሊያም ስታተስ ባስገቡበት ቋንቋ ሁልጊዜ መዘዝ ይከተላቸዋል። ለምሳሌ በማኬሬሬ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶ/ር ስቴላ ኒያንዚ የሚከተለውን ግጥም እ.ኤ.አ. በ2017 በፌስቡክ ላይ በመለጠፍ የፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቬኒን ድርጊት ተችተዋል፡

**‘Museveni matako nyo. Ebyo byeyayogedde e Masindi yabadde ayogera lutako.’**

**ሲተረጎምም**

**‘ሙሴቬኒ ልክ እንደ መቀመጫዎች ነው፡ በማሲንዲ በሚናገርበት ጊዜም እንደ መቀመጫዎች ይናገር ነበር’’ (ኒያንዚ, 2017).**



Stella Nyanzi
January 27, 2017 ·

Museveni matako nyo! Ebyo byeyayogedde e Masindi yabadde ayogera lutako.

I mean, seriously, when buttocks shake and jiggle, while the legs are walking, do you hear other body parts complaining? When buttocks produce shit, while the brain is thinking, is anyone shocked? When buttocks fart, are we surprised?

That is what buttocks do. They shake, jiggle, shit and fart. Museveni is just another pair of buttocks. Rather than being shocked by what the matako said in Masindi, Ugandans should be shocked that we allowed these buttocks to continue leading our country. Matako butako.

3.9K 2.2K Comments 1.2K Shares

Share

ከዚህ በኋላ ኒያንዚ በ2011 በኮምፒዩተር አላግባብ መጠቀም ህግ መሰረት በሳይበር ትንኮሳ እና አፀያፊ ግንኙነት ተይዛ ተከሳለች (ሩኮንዶ, 2018)። ኒያንዚ ሉጋንዳን እንደ የቃላት ግጥማዊ ጨዋታ ትጠቀማለች ከዚህ በተጨማሪም የራሷን የግንኙነት መረብ ለመምረጥ እና ማንኛውንም የማይስማሙ ሀሳቦችን ወይም ትርጓሜዎችን ለማስወገድ በሚሞክር መልኩ የራሷን ይዘት ለመምረጥም ትጠቀምበታለች። ሆኖም ግን፣ በኡጋንዳ አሁን ባለው የዲጂታል አምባገነንነት ፣ የኡጋንዳ ሕገ መንግሥት የዜጎችን ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ቢጠብቅም፣ ማንኛውም ቋንቋ ከመንግሥት ፖሊሲ ጋር ፊት ለፊት ይጋፈጣ

ዲጂታል መድረኮች በአህጉሪቱ እና በኡጋንዳ ውስጥ የእውቀት ምርት፣ የፈጠራ አገላለጽ እና ግንኙነት በሚሰፋበት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አንባቢዎችን በማገናኘት ላይ ናቸው (ነስቢት-አህመድ, 2017) ።ሆኖም ግን፣ ግልጽ የሆነ ክፍተት አለ፡ ዩጋንዳውያን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በመስመር ላይ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ቦታዎች እንዴት እንደሚጠቀሙበት የሚያሳይ ብዙ ሀብት የለም። በኡጋንዳ ያለው የቋንቋ ብዛት የሚያመለክተው እንደ ሉጋንዳ ያሉ ቋንቋዎች ብቻ ዓለም አቀፍ እውቅና እየተሰጣቸው እንደሆነ ነው፣ ለምሳሌነትም በአዲሱ የጎግል ትርጉም በኩል ያለውን እውቅና ማንሳት ይቻላል (ባምቢኖ, 2022) ።ነበተለይም የሰሜን ባንቱ ያልሆኑት ቋንቋዎች ወደ መውደቁ ናቸው። በዲጂታል መድረኮች እየበለጸጉ ወይም ደግሞ እየተጠኑ አይደሉም።

# የቅኝ ግዛትና የቋንቋ ውርስ በበይነመረብ ላይ

አንድ ሰው የሚናገረው ቋንቋ(ዎች) ከዲጂታል ዓለም ጋር በሚኖረው ግንኙነት እና ተደራሽነቱ ላይ ተጨባጭ ተፅዕኖ አለው። ይህም በቀጥታ ከእኩል ያልሆነ የዲጂታል መብቶች ስርጭትን የተመረኮዘ ነው። ይህም በመረጃ ተደራሽነት እና የአገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ዕድገት ተደራሽነት ላይ ይታያል። ከኢኮኖሚ አንጻር ክፍተት ያለባቸው ሰዎች ሃሳባቸውን ቀጥታ በበይነ-መረብ ላይ ለመግለጽ በተለየ ሁኔታ ተጨማሪ ችግር እንደሚሆንባቸው ጥሬ ሃቅ ነው። የአገሬው ተወላጅ ዕውቀትም ተሰርዞ የበላይ ወይም ብዙ ቋንቋ እና አገላለፅ ባለው ተተክቷል።

ከላይ እንደተገለፀው አብዛኛው ውይይት ተመልሶ የሚገናኘው ያኔ ከነበረው የቅኝ ግዛት ዘመን  እንዴት በቀጥታ ወደ አዲስ ወደሆነው የዲጂታል ቅኝ ግዛት እንዳደገ ነው።
ክዌት (2016) ዲጂታል ቅኝ ግዛትን የአሜሪካ እና ሌሎች የምዕራባውያን ሁለገብ ዜጐች ዲጂታል ሃይልን ወደ ኮርፖሬሽኖች በማሰባሰብ በዓለምአቀ ላይ ቁጥጥር እያደረጉ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ይህም አንዱ የቴክኖሎጂ የበላይነት መንገድ ነው። የአይሲቲ ኩባንያዎች በአብዛኛዎቹ የሶፍትዌሮች እና የዲጂታል መድረኮች ቁጥጥርን የሚያደርጉት መቀመጫቸውን አሜሪካ ላይ አድርገው ነው፡ ለምሳሌ የድር አሳሾች የፍለጋ ፕሮግራሞች፣ የማሰራጫ ጣቢያዎች፣ ወዘተ.. ። ቴክኖሎጂ በዓለምአቀፍ ሰሜናዊ ህዝቦች ለራሳቸው ህዝብ ሲመረት፣ ዓለምአቀፍ የደቡብ ማህበረሰቦች በገጠራማው አካባቢ የሚኖሩ ተወላጆች ለቴክኖሎጂው ተደራሽነት ሲሉ የኑሮ ስርዓታቸውን ለመለወጥ ይገደዳሉ (ያንግ, 2019) ። ተቺዎች ይህ ሙሉ በሙሉ በበይነ-መረብ ላይ የሚካሄደው አዲስ የኢምፔሪያሊዝም ዓይነት ነው ብለው ያምናሉ። ኃይል የሚስፋፋው በእነዚህ ቁልፍ ንብረቶች (መድረኮች) ስርጭት ነው ምክንያቱም አዲሱ የአኗኗር ዘይቤ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ወደ መሆን ይመጣሉና። ሬናታ አቪላ እንዳብራራው፣ "የዓለም ኦፍላይን ያሉ ህዝቦች የአከራካሪው የቴክኖሎጂ ኢምፓየር ግዛት ናቸው፣ ምክንያቱም ዲጂታል ፊውዳሊዝም ውስጥ እንዲገቡ ያደረጋቸው ሃገር የወደፊቱንም ቁልፍ በእጁ ይዝዋል" (ሞዚላ ፋውንዴሽን, 2018)።

ይህም በቀጥታ የሚተረጎመው በእነዚህ መድረኮች የበላይ ወደሆነው ቋንቋ እና ማን ወይም ምን እንደሚቆጣጠራቸው ነው። ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት የሚኖሩ ብዙ ሰዎች ኢንተርኔት የሚጠቀሙት በአገሬው ተወላጅ (በራሳቸው) ቋንቋዎች ሳይሆን በቅኝ አገዛዝ የተጫነባቸው ቋንቋ ነው (ሙያድዚዋ እና ምንስዋንጎ ,2021)።  እንደ ሜታ (በቀድሞው ስሙ ፌስቡክ) ያሉ ኩባንያዎች እንደ ፍሪ ቤዚክስ ያሉ "ቀለል ያሉ" መተግበሪያዎች (አፕሊኬሽኖችን) በሰፊው ታዋቂ አድርገዋል ነገር ግን በስተመጨረሻ የተለያዩ የህዝብ ቡድኖችን የቋንቋ ፍላጎቶች አያሟሉም (ሶሎን, 2017) ።  ምንም እንኳን ስዋሂሊ በሰፊው የሚነገር ቢሆንም ኬንያውያን መሰረታውያኖቹን በእንግሊዝኛ ብቻ ነው ማግኘት የሚችሉት። በምዕራባውያን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ብቻ ቁጥጥር የሚደረግበት በይነ-መረብ ትኩረቱ ፍላጎት፣ አቅርቦት እና ኃይል ላይ ብቻ ነው። ይህም ትኩረት የአብዛኛውን የዓለም ሕዝብ ፍላጎት ያላገናዘበ ነው። ከዚህም የተነሳ ፣ ከሰሃራ በታች ባሉ አፍሪካ እና አብዛኛው የዓለም ደቡባዊ ክፍል የቋንቋ አጠቃቀም ላይ የሚደረገው ጥናት በአብዛኛው የሚያተኩረው በቅኝ ገዥ የቋንቋ አጠቃቀም (ፈረንሳይኛ፣ ፖርቱጋልኛ እና እንግሊዘኛ) ላይ ሲሆን ይህም የአገሬው ተወላጅ ቋንቋ ምርምርን አቅጣጫ ችላ በማለት ነው ፡፡ (ሻባንጉ እና ሳላዉ, 2021) ።

# የእርምጃ ጥሪ

በሁሉም ዘርፍ ያሉ የዲጂታል መድረኩን ባንድም ሆነ በሌላ በኩል የሚጠቀሙ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የበለጠ አካታች እና የተለያየ የቋንቋ ያለበት መድረክን መፍጠር አለባቸው። ይህም፡-

ፖሊሲ አውጪዎች እና መንግስታት፡-
- የክፍት የኮድ ምንጭ ማዘዝ
- በአገር ውስጥ ቋንቋዎች የዲጂታል ትምህርትን ማስተዋወቅ
- የቴክኖሎጂ ንግዶች በአገር ውስጥ እንዲሠሩ ማበረታታትን ያጠቃልላል።

የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች;
- የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ምላሽ/አስተያየት እንዲሰጡ የአገሬው ተወላጆችን ማማከር።
- በትውልድ አገራቸው ብዙም ያልተወከሉ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎችን መቅጠር
- በአለምአቀፋዊው ደቡብ ያሉ የኮድ አበልፃጊዎችን መተርጎም እንዲችሉ ሶፍትዌርን እና ኮድን በአካባቢያዊ kንk ማዘጋጀት
- ከላቲን ውጪ የሆኑ ፊደሎች ላይ በሶፍትዌር እና በኮድ ተጨማሪ ግብዓቶችን ማውጣት
- በሁሉም የሥራ አገሮች ውስጥ የይዘት ማጣራት ላይ ትኩረት ማድረግ

የሲቪል ማህበረሰብ፡-
- በአገሬው ተወላጆች የሚመሩ ማህበራዊ ሚዲያዎችን እና ሌሎች ዲጂታል መድረኮችን መደገፍ
- የጥናት ምርምሮችን ማካሄድ መቀጥል
- የውትወታ(አድቮኬሲ)መድረኮችንማዘጋጀት

ዓለም አቀፍ አካላት፡-
- በበይነመረብ ላይ ሊጠፉ የተቃረቡ ቋንቋዎችን ለመጠበቅ የሚያስችል የገንዘብ ድጎማዎችን ስፖንሰር ማድረግ
- የሀገር ውስጥ ድርጅቶችን መደገፍ እና ክልላዊ እና ዓለም አቀፋዊ ውትወታዎችን መስራት

# ማጠቃለያ

በዲጂታል ዓለም ላይ ያለው የመረጃ እና የቋንቋ አለመመጣጠን የቅኝ ግዛት ዘመን የመረጃ አወቃቀር እና ውክልና ሁኔታን የማጠናከር አቅም አለው። (ግርሀም እና ዙክ፣2014)። ነገር ግን፣ የዲጂታሉ ዓለምን ቋንቋ ለማጎልበት ቦታ እና ዕድልም አለ። በይነመረብ ለሁሉም ሰው ክፍት ስለሆነ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሃሳቦች እንዲስፋፉ አድርጓል። የዲጂታል መድረኩ ቋንቋዎችን ለመመዝገብ እና ለማቆየት፣ ለማጋራት፣ ለማስተማር እና መዛግቦችን ለአዲስ ወይም ነባር ተናጋሪዎች ለማሰራጨት እና ከመረጃ ለተገለሉ ቡድኖች መረጃን በመተርጎም ለማጋራት ሊጠቅም ይችላል። የዲጂታሉ ዓለም ብዙ ተናጋሪ ለሌላቸው ቋንቋዎች እንዲዳረስ በመደረጉ፣ የበይነመረብ የቋንቋ ማህበረሰቦች በተገቢው እና በተዘጋጀ ዲጂታል መድረክ ሊያድጉ ይችላሉ። የበይነመረብ ተደራሽነት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ እና ከዚህ ቀደም ተደራሽ ላልሆኑ ማህበረሰቦች ተደራሽ እየሆነ በሄደ ቁጥር በአብዛኛው ከግሎባል ደቡብ የሚገኙ የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች "የቋንቋ ልሂቃንን" ይሞግታሉ (ITU, 2021)። የዲጂታል መድረኮች በዲጂታል ምርቶች እና ዲዛይን አጠቃቀም እና ፈጠራ ላይ የተገለሉ ቡድኖችን ለማካተት ጠቀሜታ አላቸው።

በግሎባል ደቡብ በቋንቋ እና በቴክኖሎጂ ላይ ያለው የምርምር ስራዎች እጥረት ፖሊሲ(Pollicy) አሁን በሂደት ላይ ያለውን የምርምር ፕሮጀክቶች ከዲጂታል ፊውቸርስ ላብ (Digital Futures Lab) እና ከኢንተርኔት ሶሳይቲ ፋውንዴሽን (Internet Society Foundation) ድጋፍ ጋር በመተባበር እንዲሰሩ መንገድ ከፍቷል። "አብረን ነን" (Are We Together") የሚለው ፕሮጀክት በኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ፣ ኡጋንዳ እና ህንድ ውስጥ በበይነ መረብ ላይ ያሉ የቋንቋ አጠቃቀምን በመዳሰስ እና በመመዝገብ ላይ ይገኛል። ዋነኛ ዓላማው እንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑ የበይነመረብ ተጠቃሚዎች ያጋጠሟቸው እና የሚያጋጥሟቸው ፈተናዎች ምን እንደሆኑ መረዳት ነው። የተሰበሰቡትን መረጃዎች መነሻ በማድረግ፣ የእነዚህን መድረኮች ተደራሽነት፣ አጠቃቀም እና ደህንነትን ከማሻሻል አንፃር የእነዚህ መድረክ ዲዛይነሮች ምን ምን ሊተገብሩ ይችላሉ? ይህ ፕሮጀክት ብዙሀኑ ማህበረሰብ በይነ መረብን እንዴት እንደሚጠቀም፣ መረጃ እንዴት እንደሚሰበስብ እና እንደሚያነጭ የመሰሉ አጀንዳዎችን ለማጥናት ይሞክራል።

# ዋቢዎች


Adedimeji, M.A. 2004. The unifying role of English in a multilingual nation: The case of Nigeria. In O.Ndimele (ed.), Language and Culture in Nigeria: A Festschrift for Essen Okon, 67-86. Aba: National Institute for Nigerian Languages.

Anthony, D., & Mutalemwa, D. K. (2014). Factors influencing the Use of Mobile Payments in Tanzania: Insights from Zantel's Z-pesa services. Journal of Language, Technology & Entrepreneurship in Africa, 5(2), 69-90.

Ayalew, Y.E. (2021). Uprooting Hate Speech: The challenging task of content moderation in Ethiopia. Open Internet. URL:
https://openinternet.global/news/uprooting-hate-speech-challenging-task-content-moderation-ethiopia

Bambino, R. (2022) Luganda added to Google translate using a new machine learning technique. TechJaja. Published 12 May 2022. Retrieved 12 June 2022 from
https://techjaja.com/luganda-added-to-google-translate-using-new-machine-learning-technique/

Batibo, H. (2005) Language Decline and Death in Africa: Causes, Consequences and Challenges. Clevedon: Multilingual Matters.

Batibo, H. M. (1995). The growth of Kiswahili as the language of education and administration in Tanzania. CONTRIBUTIONS TO THE SOCIOLOGY OF LANGUAGE, 69, 57-57.

Buliva, A. (2017). Machine Natural Language Translation Using Wikipedia as a Parallel Corpus: A Focus on Swahili(Doctoral dissertation, United States International University-Africa).

Ethiopia Constitution. (1995) Constitution of the Democratic Republic of Ethiopia.

Ethiopia Ministry of Education. (1994) 'National Education and Training Policy (NETP)'.

Gereme, F., Zhu, W., Ayall, T., & Alemu, D. (2021). Combating fake news in "low-resource" languages: Amharic fake news detection accompanied by resource crafting. Information, 12(1), 20.

Gerencheal, B. (2016). Gender Differences in Foreign Language Anxiety at an Ethiopian University: Mizan-Tepi University Third Year English Major Students in Focus. Online Submission, 1(1), 1-16.

Gerencheal, B., & Mishra, D. (2019). Foreign Languages in Ethiopia: History and Current Status. Online Submission, 6(1), 1431-1439.

Getachew, S. (2020). Ethiopia is adding four more languages to Amharic as political instability mounts . Hiiraan. Link:
https://www.hiiraan.com/news4/2020/Mar/167325/ethiopia_is_adding_four_more_official_languages_to_amharic_as_political_instability_mounts.aspx

Getachew, A., & Derib, A. (2006). Language policy in Ethiopia: History and current trends. Ethiopian journal of education and sciences, 2(1).

Christison, M., & Murray, D. E., (2014). What English language teachers need to know: Designing curriculum. (Vol. 3). New York: Routledge.

Coleman, D. (2018). Digital colonialism: The 21st century scramble for Africa through the extraction and control of user data and the limitations of data protection laws. Mich. J. Race & L., 24, 417.

Gerencheal, B., & Mishra, D. (2019). Foreign Languages in Ethiopia: History and Current Status. Online Submission, 6(1), 1431-1439.

Graham, M., & Zook, M. (2013). Augmented realities and uneven geographies: exploring the geolinguistic contours of the web. Environment and Planning A, 45(1), 77-99.

Cullen, R. (2001). Addressing the digital divide. Online information review.

Galperin, E. (2014). How To Enable Amharic In Google Docs, And Why It Matters To Ethiopian Bloggers. Electronic Frontier Foundation. Link:
https://www.eff.org/deeplinks/2014/05/how-switch-languages-amharic-google-drive-docs-and-other-google-products

Habtu, A. (2003). Ethnic federalism in Ethiopia: Background, present conditions and future prospects.

Halvorsen, T. A. (2012). Participation in the ICT era: Implementation without humiliation, misconception and false consciousness. International Review of Education, 58(3), 313-334.

Hogan, C. (1999). OCR for minority languages. In Symposium on Document Image Understanding Technology.

International Telecommunication Union (2021). Measuring digital development: Facts and figures, 2021.

ITU Publications. Retrieved 12 June 2022 from
https://www.itu.int/en/ITU-D/Statistics/Documents/facts/FactsFigures2021.pdf

Kafyulilo, A. (2014). Access, use and perceptions of teachers and students towards mobile phones as a tool for teaching and learning in Tanzania. Education and Information technologies, 19(1), 115-127.

Kakungulu-Mayambala, R., & Rukundo, S. (2019). Digital activism and free expression in Uganda. African Human Rights Law Journal, 19(1), 167-192.

Kamau, S. N. (2007). A digital divide: Kiswahili holds the key. Journal of Language, Technology & Entrepreneurship in Africa, 1(1), 133-143.

Kasozi, A.B.K. (2000). The failure to develop a national language in Uganda: A historical survey. In K.Parry (ed.), Language and Literacy in Uganda: Towards a Sustainable Reading Culture, 23-29. Kampala: Fountain Publishers.

Kemp, S. (2021). Digital 2021: Ethiopia. DataReportal.
Link: https://datareportal.com/reports/digital-2021-ethiopia

Kenaw, S. (2017). Cultural translation of technologies in Ethiopia. Ethiopian Journal of the Social Sciences and Humanities, 13(2), 109-142.

Kibona, L., & Rugina, J. M. (2015). A review on the impact of smartphones on academic performance of students in higher learning institutions in Tanzania. Journal of Multidisciplinary Engineering Science and Technology (JMEST), 2(4), 673-677.

Kornai, A. (2013). Digital language death. PloS one, 8(10), e77056.

Kubitschko, S., & Kaun, A. (Eds.). (2016). Innovative methods in media and communication research. Cham: Springer International Publishing.

Kwet, M. (2022). Digital colonialism is threatening the Global South. Al Jazeera. Retrieved 13 May 2022, from https://www.aljazeera.com/opinions/2019/3/13/digital-colonialism-is-threatening-the-global-south.

Kwet, M. (2019). Digital colonialism: US empire and the new imperialism in the Global South. Race & Class, 60(4), 3-26.

Legère, K. (2006). Formal and informal development of the Swahili language: Focus on Tanzania. In Selected proceedings of the 36th annual conference on African linguistics (pp. 176-184). Somerville, MA: Cascadilla Proceedings Project.

Manyerere, D. J. (2021). ICT and economic empowerment: analysing how youth in Tanzania use social

media to facilitate income-generation activities. 898111358.

Mapunda, G., & Gibson, H. (2022). On the suitability of Swahili for early schooling in remote rural Tanzania: do policy and practice align?. Journal of the British Academy, 10(s4), 141-168.

Mapunda, G., & Rosendal, T. (2021). Imagined Futures and New Technology: Youths' Language Attitudes in Songea, Tanzania. Language Matters, 52(1), 92-112.

Mapunda, G. (2013). African philosophy of management in the context of African traditional cultures and organisational culture: the case of Kenya and Tanzania. Philosophy of Management, 12(2), 9-22.

Mazrui, A. A., Mazrui, A. A. M., & Mazrui, A. M. (1998). The Power of Babel: language and governance in the African experience. University of Chicago Press.

Mazrui, A. A., & Mazrui, A. M. (1995). Swahili state and society: The political economy of an African language. East African Publishers.

Megerdoomian, K., & Parvaz, D. (2008). Low-density language bootstrapping: the case of Tajiki Persian. In Proceedings of the Sixth International Conference on Language Resources and Evaluation (LREC'08).

Mozilla Foundation (2018). Resisting digital colonialism. Internet Health Report 2018. Retrieved 10 June 2022, from,: https://internethealthreport.org/2018/resisting-digital-colonialism/

Munyadziwa, M.A. & Mncwango, E.M. (2021) Promoting the Use of Indigenous Languages on Social Media. International Journal of Research and Innovation in Social Science (IJRISS), 5 (5), 310 - 314.

Murthy, D. (2008). Digital ethnography: An examination of the use of new technologies for social research. Sociology, 42(5), 837-855.

Mwansoko, H. (1991). Swahili Terminological Modernization in Tanzania. What Are the Register Users' Views?. Meta: journal des traducteurs/Meta: Translators' Journal, 36(1), 301-310.

Mwapwele, S. D., & Roodt, S. (2016). The extent of usage of mobile devices for learning outside the classroom in a secondary school in Tanzania.

Mziray, P. R. (2019). Evaluating the acceptance and descriptive usability of the Swahili coined terminologies: An investigation of the ICT terminologies. International Journal of Linguistics, Literature and Translation, 2(6), 447-455.

Nabende, P., Kabiito, D., Babirye, C., Tusiime, H., & Nakatumba-Nabende, J. (2021). Misinformation detection in Luganda-English code-mixed social media text. arXiv preprint arXiv:2104.00124.

Namasinga Selnes, F., & Orgeret, K. S. (2020). Social media in Uganda: revitalising news journalism?. Media, Culture & Society, 42(3), 380-397.

Nesbitt-Ahmed, Zahrah (2017). Reclaiming African literature in the digital age: an exploration of online literary platforms, Critical African Studies, 9:3, 377-390, DOI: 10.1080/21681392.2017.1371618

Norton, B. (2015). Identity, Investment, and Faces of English Internationally. Chinese Journal of Applied Linguistics, 38(4). doi:10.1515/cjal-2015-0025

Nyanzi, S. (2017) 'Facebook Post,' Facebook. Retrieved on 12 June 2022 from https://www.facebook.com/stella.nyanzi/posts/10154878225000053

Obondo, M.A. (2007). Tensions between English and mother tongue teaching in post-colonial Africa. In J.Cummins and C.Davison (eds), International Handbook of English Language Teaching, 37-50. New York, NY: Springer.

Oluwole, V. (2021). M-Pesa Africa active users reach 50 million in 2021. Business Insider Africa. Link: https://africa.businessinsider.com/local/markets/m-pesa-africa-active-users-reach-50-million-in-2021/jw43zef

Parks, L., & Thompson, R. (2020). Internet Shutdown in Africa| The Slow Shutdown: Information and Internet Regulation in Tanzania From 2010 to 2018 and Impacts on Online Content Creators. International Journal of Communication, 14, 21.

Pellet, P. (2021). Understanding the 2020-2021 Tigray Conflict in Ethiopia–Background, Root Causes, and Consequences. KKI ELEMZÉSEK, 2021(39), 1-20.

Perez, S. (2017). Google's voice typing tech adds support for 30 more languages, reaching further into Africa, India. Techcrunch.
Link: https://techcrunch.com/2017/08/14/googles-voice-typing-tech-adds-support-for-30-more-languages-reaching-further-into-africa-india/

Rosendal, T., & Mapunda, G. (2014). Is the Tanzanian Ngoni language threatened? A survey of lexical borrowing from Swahili. Journal of Multilingual and Multicultural Development, 35(3), 271-288.

Rosendal, T. (2016). Language transmission and use in a bilingual setting in rural Tanzania. Endangered Languages and Languages in Danger, 335.

Rukundo, S. (2018). "My President is a Pair of Buttocks": the limits of online freedom of expression in Uganda. International Journal of Law and Information Technology, 26(3), 252–271. doi:10.1093/ijlit/eay009

Rubagumya, C. M. (1990). Language in Tanzania. Language in education in Africa: Tanzanian

perspectives, 5-14.

Rumanyika, J., Tedre, M., Apiola, M., Oyelere, S. S., & Mramba, N. R. (2019). Contemporary Challenges in Street Trader-Customer Interaction Through Mobile Devices in Dodoma, Tanzania. In International conference on social implications of computers in developing countries (pp. 76-88). Springer, Cham.

Sasikumar, M., & Hegde, J. J. (2004). Software localisation: some issues and challenges. In SCALLA conference, Kathmandu available from CDAC, Mumbai (formerly NCST).

Shahbaz, A. and Funk, A. (2020). Freedom On The Net 2020: The Pandemic's Digital Shadow. Freedom House.
Link: https://freedomhouse.org/sites/default/files/2020-10/10122020_FOTN2020_Complete _Report_-FINAL.pdf

Sharma, G. (2013). English in Ethiopia. Science, Technology and Arts Research Journal, 2(1), 74.

Shikali, C. S., & Mokhosi, R. (2020). Enhancing African low-resource languages: Swahili data for language modelling. Data in brief, 31, 105951.

Siminyu, K., Amran, K. M., Karatu, A. N., Resani, M., Junior, M. M., Ryakitimbo, R., & Mwasaru, B. (2022). Corpus Development of Kiswahili Speech Recognition Test and Evaluation sets, Preemptively Mitigating Demographic Bias Through Collaboration with Linguists. In Proceedings of the Fifth Workshop on the Use of Computational Methods in the Study of Endangered Languages (pp. 13-19).

Simons, G. F., Thomas, A., Gibson, M., & Kornai, A. (2017). A Scale for Assessing Digital Language Vitality. In An Extended Abstract Submitted to ComputEL-2: A Workshop on Computational Methods for Endangered Languages, Honolulu, Hawaii.

Smith, L. (2008). The politics of contemporary language policy in Ethiopia. Journal of Developing Societies, 24(2), 207-243.

SOMALILAND. (2010). Ethiopia Gets Microsoft Software in Amharic.
Link: https://www.somalilandcurrent.com/ethiopia-gets-microsoft-software-in-amharic/

Ssentanda, M., & Nakayiza, J. (2015). English rules in Uganda, but local languages shouldn't be sidelined. The Conversation. Retrieved 12 June 2022, from
https://theconversation.com/english-rules-in-uganda-but-local-languages-shouldnt-be-sidelined-49381.

Taye, B. A. (2017). Ethnic federalism and conflict in Ethiopia. African journal on conflict resolution, 17(2), 41-66.

Tembe, Juliet, and Bonny Norton. "English education, local languages and community perspectives in

Uganda." Dreams and realities: Developing countries and the English language (2011): 117-140.

Thobias, R. (2019). Assessment of social media impact to Tanzania youth a case study of Dar-es-salaam (Doctoral dissertation, Mzumbe University).

Tsegaye, G., & Atnafu, S. (2016). Local Web Content Observatory System: The Case Ethiopian Languages on the Web. In Ethiopian Information and Communication Technology Annual Conference 2016 (pp. 36-40).

Tsvetkov, Y. (2017). Opportunities and challenges in working with low-resource languages. In Carnegie Mellon Univ., Language Technologies Institute.

UNICE. (2016). Ethiopia, The Impact of Language Policy and Practices on Children's Learning: Evidence from Eastern and Southern Africa. UNICEF: New York. Link: https://www.unicef.org/esa/sites/unicef.org.esa/files/2018-09/UNICEF-2016-Language-and-Learning-Ethiopia.pdf

UNICEF. (2017). Tanzania, The impact of language policy and practice on Children's learning: Evidence from Eastern and Southern Africa. UNICEF: New York.
Link: https://www.unicef.org/esa/sites/unicef.org.esa/files/2018-09/UNICEF-2017-Language-and-Learning-Tanzania.pdf

Uwezo Tanzania. (2017). Are Our Children Learning? Uwezo Tanzania Annual Learning Assessment Report 2017.
Link: https://twaweza.org/wp-content/uploads/2021/05/Tanzania-Report-2017-Web-Version.pdf

Wa Thiong'o, N. (1986). Decolonising the mind: The politics of language in African literature. East African Publishers.

Wandera, A. S. (2014). Evaluating the acceptance and usability of Kiswahili localised mobile phone app in Kenya: a case of M-Pesa app (Doctoral dissertation, University of Nairobi).

Whitley, W.H. (1969). Swahili: The rise of a national language. London: Methuen.

Woldemariam, H., & Lanza, E. (2014). Language contact, agency and power in the linguistic landscape of two regional capitals of Ethiopia. International Journal of the Sociology of Language, 2014(228), 79-103.

World Bank. (2020). Individuals using the Internet (% of population) - Ethiopia.
Link: https://data.worldbank.org/indicator/IT.NET.USER.ZS?locations=ET

Young, H. (2014). The Digital Language Divide. The Guardian. Retrieved 12 June 2022, from

http://labs.theguardian.com/digital-language-divide/#:~:text=The%20relationship%20between%20language%20and,you%20behave%20in%20these%20communities.

Young, J. C. (2019). The new knowledge politics of digital colonialism. Environment and Planning A: Economy and Space, 0308518X1985899. doi:10.1177/0308518x19858998

Yusuf, S. (2019). Drivers of ethnic conflict in contemporary Ethiopia. Institute for Security Studies Monographs, 2019(202), v-46.

Zaugg, I. A. (2020). Digital inequality and language diversity: An Ethiopic case study. In Digital Inequalities in the Global South (pp. 247-267). Palgrave Macmillan, Cham.